በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ቢሮ

## የስኬች ፕላን ማዘጋጃ እና ትግበራ ሞዴል ማንዋል ቁጥር 24/2008



ሰኔ 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

PRINTED BY YARED PRINTING +251 911 241052

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ክትትል ቢሮ

### የስኬች ፕላን ማዘጋጃ እና ትግበራ ሞዴል ማንዋል ቁጥር 24/2008

ሰኔ 2008 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ይዘት


**የምህፃረ - ቃላት ዝርዝር** .......... I

**የፅንሰ - ሀሳቦች ትርጉም** .......... I

**ክፍል አንድ. መነሻ ሀሳቦች** .......... 1

1. መግቢያ .......... 1

1.1. መነሻ .......... 1

1.2. የማንዋሉ አስፈላጊነት .......... 5

1.3. የማናዋሉ ጥቅል እና ዝርዝር ዓላማ .......... 6

1.3.1. ጥቅል ዓላማ .......... 6

1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች .......... 6

1.4. የሚጠበቁ ውጤቶች .......... 6

1.5. የማንዋሉ አተገባበር .......... 8

1.6. የተፈጻሚነት ወሰን .......... 8

**ክፍል ሁለት. የማንዋሉ አወቃቀር** .......... 8

2.1. የማንዋሉ ይዘት .......... 8

2.2. የትርጉምና ጽንሰ ሀሳብ ዳሰሳ .......... 9

2.2.1. የከተማ ፕላን ምንነት? .......... 9

2.2.2. የስኬች ኘላን (Sketch Plan) ምንነት .......... 9

2.3. የሀገር ውስጥ ተሞክሮዎች .......... 10

2.3.1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ .......... 10

2.3.2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ .......... 14

2.3.3. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ .......... 19

2.3.4. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ .......... 22

2.3.5. ከክልሎች የተገኙ ጠቃሚ ልምዶች .......... 26

2.4.የገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን ዝግጅት መሰረታዊ መርሆዎች .......... 27

2.5. የገጠር የልማት ማዕከላት የስኬች ፕላን ዝግጅት ምዕራፎች/Phases/ .......... 29

2.5.1 ምዕራፍ/Phase/ 1. የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ .......... 30

2.5.2. ምዕራፍ/ Phase/ 2. መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማደራጀት .......... 35

2.5.3. ምዕራፍ/ Phase/ 3. መረጃዎችን ማጠናቀር እና መተንተን ...............42
2.5.4. ምዕራፍ/ Phase/ 4. የስኬች ፕላኑ ፅንሰ-ሃሳብ ማዕቀፍ ማዘጋጀት..........46
2.5.5. ምዕራፍ/ Phase/ 5. ዋናውን የስኬች ፕላን ማዕቀፍ ማዘጋጀት............48
2.5.6. ምዕራፍ/ Phase/ 6. ፕላኑን ማስፀደቅ.......................................56
2.5.7. ምዕራፍ/ Phase/ 7. ፕላኑን መተግበር፣ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ...57
ክፍል ሦስት. ተያያዥ ሕጎችና ማንዋሉን የማስተግበር አቅም.......................63
3.1.የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች.........................................................63
3.1.1 የከተማ ልማት ፖሊሲ..........................................................63
3.1.2 የከተማ ፕላን ህግ................................................................64
3.1.3. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር ስትራቴጂ..............................65
3.1.4. የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ........................................66
3.2. ማንዋሉን ለማስተግበር የሚያስፈልገው የማስፈጸም አቅም ዝርዝር................67
3.2.1 . የሰው ሃይል.......................................................................67
3.2.2. ለስራው አስፈላጊ የሆነውን ሃይል ማደራጀት እና መመደብ ................68
3.2.3. አደረጃጀት.........................................................................68
3.2.4. ማንዋሉን ለመተግበር ተፈላጊው የቴክኖሎጂ ድጋፍ...........................69
3.2.5. የስኬች ፕላን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር አስፈላጊው የጊዜ መጠን.........69
ክፍል አራት.የማንዋሉ አፈጻጸም ደረጃ.............................................70
4.1.ማንዋሉ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ...............................................70
4.2. ማንዋሉን ስለማሻሻል..............................................................70
ማጣቀሻዎች ...............................................................................I
አዝሎች....................................................................................III
አዝል 1 ፦ ለገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን ለማዘጋጀት የሚረዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆች/ቸክ-ሊስቶች፣..........................................III
አዝል 2 - መረጃዎችን ለመተንተን የምንጠቀምባችው ፎርሙላዎች..........................IX
አዝል 3 ፦ ለተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ድልድል የቦታ ምርጫ መስፈርት.....................XI

የሰንጠረዦች ዝርዝር

ሰንጠረዥ1. በኦሮሚያ የገጠር የልማት ማዕከላትፕላን ዝግጅት ቡድን አንደኛው አማራጭ....11
ሰንጠረዥ2. ለገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች ድርሻ..49
ሰንጠረዥ3. የዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች የፊደላትና የቀለማት ምልክቶች.........52

## የምህፃረ-ቃላት ዝርዝር

**እ.አ.አ** - እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር

**ኢ.ፌ.ዴ.ሪ** - የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**ከ.ል.ኮ.ሚ** - ከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

**FAO -** United Nations **Food** and Agricultural Organization

**MUDC** – Ministry of Urban Development and construction

**NUPI** – National Urban Planning Institute

**UN** - United Nations

## የፅንሰ -ሃሳቦች ትርጉም

**የገጠር የልማት ማዕከል** - የህዝብ ቁጥራቸው ከ500-1999 የሆኑ ከተማ ቀመስ የሰዎች መኖሪያ አካባቢ ሆነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሁለት ሺ የህዝብ ቁጥር በላይ ኖሮዋቸው ወደመደበኛ ከተማነት ይሸጋገራሉ ተብሎ የሚገመቱ እና የነዋሪዎቹ መተዳደሪያ በአብዛኛው ግብርና ሆኖ በቀላል የማይገመት ቁጥር ያለው ነዋሪም በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ማለትም ወፍጮ ቤቶች፣ ሸቀጣሸቀጥ፣ የአካባቢ መጠጥ ቤቶች፣ ዕደጥበባት የመሳሰሉት የሚገኙባቸውና በውስጣቸውም በአቅራቢያቸው ላሉ የገጠር ቀበሌዎች የአገልግሎት መስጫ ማዕከል በመሆን የሚያገለግሉ ዋናዋና ማህበራዊ አገልግሎቶች ማለትም የገጠር ቀበሌ አስተዳደር፣ የገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም፣ ጤና ተቋማት፣ ት/ቤቶች እና የመሳሰሉት የሚገኙባቸው አካባቢዎች ናቸው፡፡

**ከተማ** - ከተማ ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም ሁለት ሺ እና ከዚያ በላይ የህዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ ሃምሳ በመቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነው የሰው ሃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ሥራ ላይ የተሰማራ ህዝብ የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡

**ስኬች ፕላን** - ስኬች ኘላን ለፈርጅ ስድስት ከተማ ቀመስ የገጠር የልማት ማዕከላት ከ5-10 ዓመት ለሚሆን የኘላን ዘመን በ1:5,000 መስፈርት የሚዘጋጅ ኘላን ነው፡፡ ይህም ፕላን ሥልጣን ባለው አካል የፀደቀና ህጋዊ ተፈፃሚነት ያለው የገጠር ማዕከሏ ስኬች ፕላን ሲሆን አባሪ የፁሑፍ ማብራሪያዎችንይጨምራል፡፡

**ፈርጅ ስድስት ከተሞች፡-** የህዝብ ቁጥራቸው ከ2000 በታች ሆነው ጥንስስ ከተሞች ሊባሉ የሚችሉ የገጠር የልማት ማዕከላት ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ. መነሻ ሀሳቦች

## 1. መግቢያ

### 1.1. መነሻ

እንደ አፍሪካ ያሉ ታዳጊ አገሮች የከተሜነት የዕድገት ደረጃ ዝቅተኛ (39.6%) ቢሆንም የከተማ የዕድገት ፍጥነት ግን ከፍተኛ (2.43%) ነው፡፡ የኢትዮጵያ የከተማነት ታሪክም የሚያሳየው ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ እስካሁን ያለውን የሀገራችን የከተማ ህዝብ እድገት ምጣኔ ስንመለከት ከ3.54% እስከ 6.11 % እንደሆነ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ ያሳያል፡፡ ይህ የዕድገት ምጣኔ አሀዝም ከሳሃራ በታች ካሉ አገሮች የከተሜነት አማካይ የእድገት ምጣኔ (4.58) የተቀራረበ ሆኖ በዓለማችን ግን ከፍተኛ ከሚባሉት ጎራ እንደሚመደብ አሃዙ ይጠቁማል፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት ሶስት አሥርት አመታት ውስጥ የሀገሪቱ የከተማ ነዋሪው ህዝብ በአራት እጥፍ በማደግ በ1958 ዓ.ም. ከነበረበት 1.5 ሚሊዮን በ1999 ዓም ወደ 11.9 ሚለዮን የደረሰ ሲሆን(የከ.ል.ኮ.ሚ፣ 2003) የተባበሩት መንግስታት የሥነ-ህዝብ ክፍል በዓለም አገሮች የህዝብ ብዛት ትንበያ መረጃ እንደገለፀው በ2008 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት ወደ 101,117,886 የደረሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 81,905,487 (81 በመቶ) የሚሆነው በገጠር ሲኖር ቀሪው 19,212,398.34 (ወደ 19 በመቶ) በከተሞች የሚኖር ነው (United Nations, 2016)፡፡ በዚሁ መሰረት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን ማብቂያ (በ2012) በከተማ የሚኖረው የህዝብ ድርሻ 25 በመቶ እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ በተመሳሳይ የሃገራችን የአከታተም ደረጃ በሶስተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን መጨረሻ ወይም አገራችን መካከለኛ ገቢ

ያላቸው ሃገራት የደረሱበት ደረጃ በምትደርስበት ዓመት (2017) አሁን ካለንበት (20 በመቶ) ወደ 30 በመቶ፣ በ2022 ዓ.ም ደግሞ 35 በመቶ እና በ2027 40 በመቶ ሊደርስ እንደሚችል የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር በሃገራዊ የከተማ ልማት እና የህዝብ አሰፋፈር ፕላን ጥናት አመልክቷል (MUDH, 2016)።

በኢትዮጵያ የከተሞች እድገት እየታየ ያለው በነባር ከተሞች መስፋፋት እና የህዝብ ቁጥር መጨመር ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በአጭር ጊዜ ውስጥ የህዝብ ቁጥራቸው እየጨመረ እና የኢኮኖሚ፣ ፖሊቲካዊ እና አስተዳደራዊ መዋቅራቸው እያደገ መጥቶ ወደ ከተማነት እየተለወጡ በመሆናቸውም ጭምር ነው። በአሁኑ ጊዜ የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚ/ር መረጃ የሚያሳየው ቀደም ሲል በ2003 ዓ.ም በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው የከተሞች ቁጥር 971 የነበረ ቢሆንም (የከ.ል.ኮ.ሚ፣ 2003 ዓ.ም) በ2007 ዓ.ም ወደ 1565 አካባቢ የደረሰ መሆኑን ነው።

ምንም እንኳ አገሪቱ በምትከተለው የኢኮኖሚ ዕድገት አቅጣጫ ባለፉት አስር አመታት እየተመዘገበ ባለው በአማካይ የሁለት አሃዝ (10.6 %) የኢኮኖሚ እድገት እና በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ላይ ተፅእና እያመጣ ባለው ከ2003 - 2007 ዓ.ም የዕድገት ዘመን በተነደፈው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ምክንያት በሀገሪቱ ፈጣን የከተሞች እድገት እየተስተዋለ ቢሆንም በከተሞች የሚኖረው የአብዛኛው ህዝብ የመኖሪያ አካባቢዎች ያረጁ፣ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ከፊሉም የተሟላ የከተማ ፕላን በሌላቸው ቤቶች የተጨናነቁ ናቸው።

አሁን በሀገሪቱ የሚገኙ ወደ 17000-የሚሆኑ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት በአብዛኛው በፕላን እየተመሩ ባለሞሆናቸው የወደፊት የዕድገት አቅጣጫቸው በተመሳሳይ ሁኔታ የተዛባ መሆኑ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ይህ ከመሆኑ በፊት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ከተማነት ይለወጣሉ ተብለው የሚገመቱ የገጠር የልማት ማዕከላትን **ስኬች ፕላን** በማዘጋጀት በፕላን እንዲመሩ በማድረግ ቅርፅ ይዘው ወደ ከተማነት እንዲቀየሩ የማድረግ አስፈላጊነትን

የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ስትራቴጂ ውስጥ እንደ አንድ የስትራቴጂ አቅጣጫ ተቀምጧል። እንደዚሁም በገጠር ያለውን ሥርዓት ያልጠበቀ ኋላቀር እና ለኑሮ የማይመች ቤት በማሻሻል ለገጠሩ ህዝብ የተሻሻለ ዘመናዊ የገጠር ቤት ግንባታና ተያያዥነት ያላቸውን ልማታዊ አገልግሎቶችን በመንግስት እና በህዝብ ትብብር ተጠናክረው እንዲገነቡ ለማድርግ የገጠር ቤቶች ልማት ስትራቴጂ በከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር በ2008 ዓ.ም. የተቀረፀ በመሁኑ በገጠሩ የታሰበውን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን (ወደ 1.7 ሚሊዮን) የቤት ልማት በአግባቡ ለማከናወን ፕላን የመሪነቱን ሚና ሊጫወት ይገባል።

በፕላን መመራት ለህዝብ አስፋፈር፣ ለመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ፣ ለኢኮኖሚ እድገት እና ባጠቃላይ ለሁለንተናዊ እድገታቸው ቁልፍ መሆኑ በመርህ ተቀባይነት ያለው ጉዳይ ነው። የገጠሩ ህዝብ ሐብት በፕላን ላይ ተመስርቶ የሚሰራቸው ቤቶችም እንደ ዕሴት ሆኖ ለልዩ ልዩ ጉዳዮች በፋናንስ ምንጭነትም እንዲያገለግል ፕላን አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

በክልሎች በፕላን ዝግጅትና ትግበራ ውስጥ እንደ ችግር ከሚነሱ ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹ የማስፈጸም አቅም ውስንነት፣ የፕላን ዝግጅት እና አፈፃፀም ክህሎት ውስንነት፣ በቂ የሰው ሃይል አለመኖር እና ከመሳሰሉት ችግሮች ባሻገር የእነዚህ በፈርጅ ስድስት ውስጥ ላሉ የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን አዘገጃጀት እና አፈፃፀም በተመለከተ መመሪያ እና ማንዋል አለመኖር በሀገራችን ከሚታዩ ችግሮች ከብዙ ጥቂቶች በመሆናቸው እና ከላይ የተቀመጡ ዋናዋና ነጥቦች ለዚህ ማንዋል ዝግጅት መነሻ ሆኗል።

ለዚህ ማንዋል ዝግጅት የሁሉንም ክልልሎች የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ተሞክሮ ማሰባሰብ ጠቃሚ ቢሆንም ካለው የሃብት ውስንነት አንፃር ከተወሰኑ ክልሎች ማለትም ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከትግራይ እና ከደቡብ በተወሰደ ጠቃሚ ልምድ

እና ተሞክሮ እንደዚሁም የመሬት አጠቃቀም ፕላን ማዘጋጃ ጠቃሚ ሰነዶችን በማጣቀስ ማናዋሉ ለሁሉም ክልሎች በሚጠቅም መልኩ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 1.2. የማንዋሉ አስፈላጊነት

የገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን ማዘጋጃ ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ከሚሆኑባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ዋና ዋናዎች ናቸው፡፡

1.2.1. በሀገራችን በየጊዜዉ ወደ ከተማነት የሚቀየሩ ወደ 17000 የሚሆኑ የገጠር የልማት ማዕከላት እየጨመረ መምጣት እና እነዚህ ማዕከላት በፕላን እንዲመሩ የከተማ ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ስትራትጂያችን የትኩረት አቅጣጫ መሆኑ፣

1.2.2. አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የገጠር የልማት ማዕከላት በፕላን የማይመሩ በመሆናቸዉ በአካባቢያቸዉ ያለዉን ለም የእርሻ መሬት እና በደን የተሸፈነ መሬት በመሻማት ለአካባቢ ሥነ-ምህዳር መዛነፍ ምክንት እየሆኑ በመምጣታቸዉ ይህንን ከወዲሁ ለመግታት የአሁኑን ትውልድ በሃብት የመጠቀም ፍላጎት ጥያቄ ውስጥ ሳያስገባ ነገር ግን መሬትን በቁጠባ እና እሴት በሚፈጥር መልኩ እየተጠቀሙ የቀጠዩን ትውልድ በዘላቂነት የመጠቀም ዋስትና ማረጋገጥ፣

1.2.3. የገጠር ማእከላቱ ከወዲሁ በፕላን እንዲለሙ ማድረግ ወደፊት ወደከተማነት አድገው በዝርዝር የከተማ ፕላን እንዲመሩ ሲደረግ የሃብት ብክነትን ለመቀነስ ስለሚያስችል እና ለኢንቬስትመንት ምቹ ሆነው እንዲያድጉ ለማስቻል እና ሌሎችም የዚህ ማንዋል ዝግጅት ምክንያቶች ናቸዉ፡፡

1.2.4. ይህ ማንዋል በጥቂት ዓመታት ወደ ከተማነት ለመቀየር እያቆጠቆጡ ላሉ የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን አዘጋጆች፣ ተግባሪዎች፣ በየደረጃው ላሉ ውሳኔ ሰጪዎች፣ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በፕላን ዝግጅት እና አፈፃፀም ሂደት ወቅት በዕለት ተዕለት የፕላን ሥራቸው እንደ አጋዥ ሆኖ የሚጠቀሙበት ከመሆኑም በላይ ማንዋሉ በሀገራችን በእነዚህ የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን አዘገጃጀት እና አተገባበር ላይ ጥናት ለሚያካሂዱ ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.3. የማናዋሉ ጥቅል እና ዝርዝር ዓላማ

### 1.3.1. ጥቅል ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዝግጅት ዋና ዓላማ ወደ ከተማነት ለሚያድጉ የገጠር የልማት ማዕከላት ዘላቂ ልማታቸውን በጠበቀ ሁኔታ ዕድገታቸውን መምራት እንዲችሉ የማዕከላቱ ስኬች ፕላን አዘገጃጀት እና አተገባበር ሂደት ላይ አጋዥ የፕላን መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

የማንዋሉ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የገጠር የልማት ማዕከላት በፍጥነት ወደ ከተማነት የሚለወጡ በመሆናቸዉ ከወዲሁ በፕላን ለመምራት፣

ለ) የገጠር ልማት ማዕከላት በፕላን እንዲመሩ በማድረግ የአካባቢ ነዋሪዎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል

ሐ) የገጠር የልማት ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ፕላን በሚዘጋጅበት ወቅት የሚተገበሩትን ዋናዋና እና ዝርዝር ተግባራት እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎችን ለማሳየት ናቸው፡፡

## 1.4. የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህ ማንዋል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ፡-

1.4.1. በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ከተማነት ለሚቀየሩ በርካታ የገጠር የልማት ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅትን እና ትግበራን በማቅለል እና ጥራት በማሻሻል የገጠር ማዕከላቱ በፕላን እንዲመሩ በማድረግ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፤

1.4.2. የቴክኖሎጂ እና የዕውቀት ሽግግር በማምጣት የሀገራችንን ህዳሴ ለማገዝ የሚከተሉትን ውጤት ያመጣል፡፡

ሀ) የገጠር የልማት ማዕከላቱ በፕላን የሚመሩ በመሆናቸው የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ዕድገት በማሻሻል የነዋሪዎችን ህይወት ይለውጣሉ፤

ለ) በእነዚህ ማዕከላት የሚታየውን የአካባቢ ሥነ-ምህዳር መከላት በማሻሻል እና ዕድገታቸውን በአግባቡ በመምራት ለአካባቢው ዘላቂ ዕድገት መሠረት ይጥላል።

ሐ) ለአካባቢው ነዋሪዎች የገበያና የአገልግሎት ማዕከል በመሆን ሁለንተናዊ ልማትን ያፋጥናሉ፣

መ) የአስተዳደር ማዕከል በመሆን የፍትህ አሠጣጥን ተደራሽ ያደርጋሉ፣ ያልተማከለ አስተዳደርንም ያጠናክራሉ፣

ሠ) መንግስት የተበታተነውን የገጠር ነዋሪ በያለበት የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት ለማድረስ የሚያወጣውን ከፍተኛ ወጭ በአንድ ማዕከል እንዲገነባ በማድረግ ያለንን ውስን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላሉ፣

ረ) የመኪና መንገድን ተከትለው በየቦታው በመቆርቆር ለመሬት ወረራ የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ለመቆጣጠር ይረዳሉ፣ ለቀጣይ መስፋፊያነት አመቺ ባልሆነ ቦታና በቅርብ እርቀት በመቆርቆር በዕርስ በዕርስ ፍክክር ተያይዘው የሚከስሙበት/ የሚቀጭጩበትን ሁኔታ ለማስቀረት ይረዳሉ፣

ሸ) ፍትሀዊ የመሰረተልማትና የአገልግሎት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ያስችላሉ፣

ቀ) የገጠሩን ነዋሪ የአኗኗር ዘይቤ ወደ ከተማነት ለመቀየር ግንባር ቀደም ሚና ይጫወታሉ፣

በ) ገጠሩና ከተማው ተደጋግፈውና ተመጋግበው እንዲያድጉ የጐላ ሚና ይጫወታሉ፣

ተ) የገጠር ነዋሪው ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ፍለጋ ከገጠር ወደ ከተማ የሚያደርገውን ረዥም ጉዞ በአካባቢው እንዲያገኝ በማድረግ ጊዜና ገንዘቡን እንዲቆጥብ ያደርጉታል፣

ቻ) ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት ምክንያት በትላልቅ ከተሞች የሚፈጠረውን ከፍተኛ የህዝብ መጨናነቅ ጫና ይቀንሳሉ፣ ወዘተ

### 1.5. የማንዋሉ አተገባበር

የገጠር የልማት ማዕከላትን ስኬች ፕላን ለማዘጋጀት እና ለመምራት የሚቋቋሙ የፕላን ቡድኖች እና የመንግስት አካላት በፕላን ዝግጅት እና አፈጻጸም ሂደት ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት እና ሙያዊ የፕላን ሥራዎችን ለማከናወን እያንዳንዱን የፕላን ዝግጅት እና አፈጻጸም ምዕራፎች ደረጃ በደረጃ ማለፍ እና ማጣቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 1.6. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ማንዋል በየክልሉ ለፕላን ሥራ በተቋቋሙ የፕላን ተቋማት እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ተፈጻሚ ሲሆን ማንዋሉ በኢትዮጵያ የመሬት ክልል ውስጥ የህዝብ ቁጥራቸው ከ2000 በታች ሆኖ በቀጣይነት በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ከተማነት ለሚሸጋገሩ የገጠር የልማት ማዕከላት የስኬች ፕላን ዝግጅት ሂደትን የሚመራ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት. የማንዋሉ አወቃቀር

### 2.1. የማንዋሉ ይዘት

ይህ ማኑዋል በአራት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል መነሻ ሐሳቦችን የያዘ ሲሆን በውስጡም መግቢያ፣ የማኑዋሉ አስፈላጊነት፣ የማኑዋሉ ጥቅልና ዝርዝር ዓላማ፣ ከማንዋሉ ዝግጅት የሚጠበቅ ወጤት፣ የማኑዋሉ አተገባበር እና የተፈጻሚነት ወሰንን ይዟል፡፡ በክፍል ሁለት ደግሞ ትርጉምና ፅንሰ ሀሳብ፣ ነባራዊ ሁኔታ፣ የተሞክሮ ዳሰሳ፣ እንዴት የስኬች ፕላን እንዴት እንደሚዘጋጅ የሚያሳዩት አስሩ የፕላን አዘገጃጀትና አፈፃፀም ምዕራፎች (phases) ተዳሰዋል፡፡ ከማኑዋሉ ጋር የተያያዙ ህጎችና ዝርዝር ትስስራቸው፤ ማኑዋሉን ለማስተግበር የሚያስፈልገው የማስፈፀም አቅም በክፍል ሶስት ስር ተገልጸዋል፡፡ ክፍል አራት ደግሞ ማኑዋሉ ተፈፃሚ የሚሆንበትን ጊዜ፣ ማንዋሉ እንዴት እንደሚከለስ፣ በማን እንደፀደቀ ይዟል፡፡

## 2.2. የትርጉምና ጽንሰ ሀሳብ ዳሰሳ

### 2.2.1. የከተማ ፕላን ምንነት?

የከተማ ፕላን የከተማ ልማት ራዕይን ለማሳካት እና በከተማዋ የሚታዩ መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት በመንግስት የአስተዳደር ሂደት ዉስጥ ወደፊት ሊሰሩ የሚገቡ ነገሮችን ቅርፅና የተሻለ የአተገባበር ሂደትን መምረጥ ማለት ነው (Bartone et al. 1994, Smith 1993)፡፡ የከተማ ፕላን የህዝብን ሐብት (ለምሳሌ መሬትን) ለመጠበቅና ለማከፋፈል እንደዚሁም ከሀብቱ የሚገኙ ጥቅሞችን በፍትሃዊነትና በአግባቡ ለማከፋፈል የሚረዳ መሳሪያ ነው (Taylor and Williams 1982)፡፡

በሌላ በኩል የከተማ ፕላን ማለት አስቀድሞ ለሚወሰን ዘመን የአንድን ከተማ እና አካባቢውን የወደፊት ዕድገት በልማታዊ ዓላማ መሰረት እንዲመራ የሚዘጋጅ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሲሆን በይዘት ደረጃ የከተማውን መሬት አጠቃቀም፣ የትራንስፖርት መስመርና ስርዓትን፣ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ የፊዚካላዊና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያካትት መሆኑን በመግለፅ የፕላኑ ውጤትም በካርታ እና በዝርዝር የፅሑፍ ሰነዶች መዘጋጀት እንደሚገባው የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ ሰነድ ተመላክቷል፡፡

### 2.2.2. የስኬች ኘላን (Sketch Plan) ምንነት

ሀ) ስኬች ኘላን ለፊርጅ ስድስት ከተማ ቀመስ የገጠር የልማት ማዕከላት ከ5-10 ዓመት ለሚሆን የኘላን ዘመን በ1፡5,000 መስፈርት የሚዘጋጅ እና ዝርዝር የመሬት አጠቃቀምን ሳያካትት ዋና ዋና የሆኑ የመሬት አጠቃቀም ምድቦችን ብቻ የሚያሳይ ሆኖ አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያመላክት ስኬማቲክ ኘላን አይነት ነው፡፡

ለ) በዚሁ መሠረት የሚዘጋጀው ኘላን የመኖሪያ አካባቢዎችን የሚያሳይና እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ለመኖሪያ የሚሰጠውን የቦታ ስፋት ተከትሎ በብሎክ ደረጃ የሚዘጋጅ፣ የገጠር ቀበሌ መስተዳድርና የፖሊስ ማዕከላት የሚያመላክት፣ ለሱቆችና የከብት ገበያ እንዲሁም ለሳምንት ገበያ የሚሆኑ ቦታዎችን የሚያሳይ፣ ለትምህርት ቤት፣ ለጤና ኬላና ለአምልኮ የሚሆኑ ቦታዎችን የሚያመላክት፣ በተለያዩ ምክንያቶች ለከተማ

አገልግሎት ሊውሉ የማይችሉ ቦታዎችን የሚያስጠብቅ እና መንገዶችን የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል (ከልቤኮሚ፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

## 2.3. የሀገር ውስጥ ተሞክሮዎች

ለዚህ ማንዋል ዝግጅት ይረዳ ዘንድ ከኦሮሚያ፣ ከአማራ፣ ከትግራይ እና ከደቡብ የከተማ ፕላን ዝግጅት ተቋማት ጠቃሚ ልምድ እና ተሞክሮ ተቀምሯል፡፡

### 2.3.1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር ማዕከላት ፕላን ዝግጅት በተሟላ ሁኔታ ለማከናወን እንዲቻል ማንዋል ያዘጋጀ ሲሆን ከማንዋሉ የተገኙትን ልምዶች እንደሚከተለው ቀርበዋል (Oromia Regional State, 2012)፡፡

**ሀ) በፕላን ቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ/ PHASE/**

**1. ፕላን የሚዘጋጅላቸው የገጠር የልማት ማዕከላት የመምረጫ ሥርዓት**

በክልሉ በኩል የገጠር የዕድገት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት ለማከናወን እንደ መነሻ የተወሰደው የግብርና መሬት እና የግብርና ምርታማነት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ መሰረተ ልማትና ገበያ እንደዚሁም የመንግስት ፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ፕላን የሚዘጋጅላቸውን የገጠር የልማት ማዕከላትን ለመከፋፈል ግምት ውስጥ የገባው መስፈርት የአባወራ/ እማወራ ብዛት /household size/ ሲሆን በሶስት ምድብ ማለትም ከ105-305፣ ከ50-104 እና ከ50 በታች የአባወራ ብዛት ያሉዋቸው የገጠር የዕድገት ማዕከላት ሲሆን አሁን ካለው የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የፋይናንስ አቅም ለሁሉም የመሬት አጠቃቀም ፕላን ማዘጋጀት ስለማይቻል በመጀመሪያ ምድብ ላሉት ቅድሚያ በመስጠት እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

## 2. የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስፈልግ የሰው ኃይል

በኦሮሚያ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት በኩል የገጠር የልማት ማዕከላትን ፕላን ለማዘጋጀት የሚያስፈልግ የሰው ኃይል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1. በኦሮሚያ የገጠር የልማት ማዕከላትፕላን ዝግጅት ቡድን አንደኛው አማራጭ**

| ተ.ቁ | የሰው ኃይል | ብዛት | አማራጭ ምንጮች | የስራ ኃላፊነት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የቅየሳ ባለሙያ | 2 | የዞን የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት | አስተባባሪ |
| | | | የዞን/የወረዳ መሬት አስተዳደርና የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤት | አባል |
| 2 | የከተማ ፕላነር፣ የከተማ መሃንዲስ፣ ከፍተኛ ቴክኒሻን (የንድፍ ባለሙያ) | 1 | « | አባል |
| | | | የኦሮሚያ የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት | አባል |
| 3 | ጂኦግራፊር፣ ኢኮኖሚስት፣ ሶስዮሎጂስት፣ የከተማ ስራ አመራር | 2 | « | አባል |
| | | | የዞን የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ጽ/ቤት | አባል |
| 4 | የቀን ሰራተኞች | 2 | የገጠር የዕድገት ማዕከል | አባል |

## ለ) በፕላን ዝግጅት ምዕራፍ/ PHASE/

### 1. መረጃ ማሰባሰብ እና ማጠናቀር

በኦሮሚያ ክልል ለገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት የሚሰበሰቡ የመሬት አቀማመጥ መረጃዎች፣ የፊዚካላዊ እና የሶሺዮ ኢኮኖሚ መረጃዎች እንደሚከተለው ተዘርዝሯል /ibid/፡፡

- የፊዚካላዊ እና የመሬት አቀማመጥ መረጃዎች
- የሶሺዮ ኢኮኖሚ መረጃዎች
- ታሪካዊ መረጃዎች
- ሥነ-ሕዝብ እና አገልግሎቶች
- የኢኮኖሚ መረጃዎች (ዝረዝሩን እዝል ሁለት ላይ ይመልከቱ)

## 2. የወሰን አከላለል ሂደቶችን ማከናወን

የገጠር የልማት ማዕከላት ወሰን የሚወሰነው ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በወረዳ እና በገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ኮሚቴዎች ነው፡፡ አማካይ የገጠር የልማት ማዕከል የቦታ ስፋት 200 ሄክታር ሲሆን ኮሚቴው በዚሁ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ ወሰኑን የሚያካልል ይሆናል፡፡ በወሰን አከላለል ጊዜ ኮሚቴው የሚከተሉትን ግምት ውስጥ ማስገባት እንደሚኖርበት ማንዋሉ ያብራራል /ibid/፡፡

- ሰሜን፣ ምስራቅ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጫፍ ያሉት የገጠር የዕድገት ማዕከላት ተፈጥሯዊ እና/ወይንም ሰው ሰራሽ ገጽታዎችን በመጠቀም መከለል ይኖርባቸዋል፤
- የገጠር የዕድገት ማዕከሉ ከገበያ እና ከማሕበራዊ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የሚኖረው ተጽዕኖ፤
- የገጠር የዕድገት ማዕከሉ በአቅራቢያ ላሉት ሰፈሮች ያለው ተስማሚነት እና ማዕከላዊነት፤
- በሁሉም አቅጣጫዎች ፊዚካላዊ ሁኔታዎችን በተመለከተ ተስማሚነት ያለው መሆኑን፤
- በአቅራቢያ ካሉ ሰፈሮች አንጻር የፊዚካላዊ እና የማሕበራዊ መሰረተ ልማቶች አቅርቦት፤
- በአካባቢው ሊኖር የሚችለው የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት፤
- በሚቀጥሉት አስር ዓመታት በገበያ፣ በመዋዕለ ንዋይ ፍሰት፣ በማሕበራዊ አገልግሎቶች፣ በመሰረተ ልማት፣ በጤና አገልግሎቶች፣ እንደዚሁም
- በትራንስፖርት መረብ ምክንያት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ሁኔታዎች፤ እና
- በገጠር የዕድገት ማዕከሉ የሚካተቱ ቦታዎች የሚኖራቸው የአካባቢያዊ እና የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ናቸው፡፡

## 3. በገጠር የልማት ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች በመለየት ፕላን ማዘጋጀት

በገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት ወቅት የሚታቀዱ ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች የሚከተሉት ናቸው /ibid/፡፡

- አጠቃላይ ገበያ እና የእንስሳት ገበያ፣
- የባህል ማዕከል፣
- የመኖሪያ ቤቶች፣
- የንግድ እና የቅይጥ አገልግሎቶች፣
- የሕዝብ እና የማህበራዊ አገልግሎቶች (በሕዝብ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚተዳደሩ)፣
- ዋና እና መለስተኛ መጋቢ መንገዶች፣
- የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች፣
- መለስተኛ ስታድዬም እና መጫወቻ ቦታዎች፣
- ጤና ኬላ፣ መዋዕለ ሕጻናት፣ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣
- የእምነት ቦታዎችና መካነ መቃብሮች፣ የአውቶብስ መነሃሪያ፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ፖስታ ቤት፣ የቴሌፎን ጽ/ቤት እና የመሳሰሉት፣
- መጋዘኖች (ለእህል ምርት እና ለማዳበሪያ)፣
- በተለያዩ የእድሜ ክልል ለሚገኙ የሚያገለግሉ መዝናኛ ቦታዎች፣ የሕዝብ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ የስፖርት ማዕከላት እና አረንጓዴ ቦታዎች፣
- ንዑስ ፖሊስ ጣቢያ፣
- ቄራ፣
- የፍሳሽ መስመሮች፣
- የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች፣ እና
- ለጋማ እንስሳት ማቆያ (በገበያ ቀን እንደዚሁም በገበያ ቀን ላልሆኑ ጊዜያት የሚያገለግል)
- የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል፡፡

## 2.3.2. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ

የገጠር የልማት ማዕከላት ትርጓሜ ከአማራ ክልል ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ በሁለት መልኩ የሚታይ ሲሆን የመጀመሪያው የነዋሪዎች መተዳደሪያ በአብዛኛው ግብርና ሆኖ የተወሰኑት በተለያዩ ጥቃቅን የሥራ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚኖሩባት ሲሆን በውስጣቸው ዋናዋና አገልግሎቶች የሚባሉ ማለትም የገጠር ቀበሌ አስተዳደር፣ የገበሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም፣ ጤና ኬላዎች፣ ት/ቤቶች ያሉባቸው አካባቢዎች ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩት ከተማ ቀመስ የገጠር ማዕከላት ሆነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደመደበኛ ከተማነት የሚሸጋገሩ እና በቀላል የማይገመት ቁጥር ያለው ነዋሪም በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ማለትም ወፍጮ ቤቶች፣ ሸቀጣሸቀጥ፣ የአካባቢ መጠጥ ቤቶች፣ ዕደጥበባት የመሳሰሉት የሚገኝባቸውና የግብርና ሥራም የሚከናወንባቸው የመኖሪያ አካባቢዎች ናቸው በማለት የ2003 ዓ.ም. የክልሉ የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የሽንሻኖ ፕላን ስልጠና ማንዋል(ያልታተመ ረቂቅ ሰነድ) አመልክቷል፡፡

እነዚህ የገጠር የልማት ማዕከላት የአጎራባች የቀበሌ ነዋሪዎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ግኑኝነት የሚካሄድባቸው እና የተለያዩ አገልግሎቶችም የሚቀርቡባቸው በመሆናቸው ዕድገታቸውን መልክና ሥርዓት ማስያዝ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ እና ለነዋሪዎች ፈጣንና ዘላቂነት ያለው አገልግሎት በአንድ ማዕከል ለመስጠት እንዲያመች ዝርዝር የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥናት ሳያስፈልገው መነሻ የሆነ የሽንሻኖ ፕላን በፕላን ተቋማት ተዘጋጅቶ በወረዳው የአካባቢ ጥበቃ እና የመሬት አስተዳደር ወደ መሬት እንዲወርድ ይደረጋል፡፡ የሽንሻኖ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ቀጥሎ በቀረቡት ምዕራፎች/ PHASES/ ይከናወናል፡፡

## ሀ) በፕላን ቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ/ PHASE/የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት

### ተግባር 1. ፕላን የሚዘጋጅላቸውን የገጠር ማዕከላትን መለየት

ለገጠር ቀበሌ የልማት ማዕከላት ፕላን እንዲዘጋጅላቸው ሲወሰን መስፈርቶቹ ለወደፊቱ የከተማ መስፋፊያነት አመች የሆነ፣ አፈሩ ለግንባታ የማያስቸግር፣ ውኃ በአቅራቢያው በቀላሉ ሊገኝበት የሚችል፣ የተዳፋት መጠኑ ከ2-16% የሆነ፣ አስተዳደራዊ እና የሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች መሰጫ ማዕከል በመሆን የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

### ተግባር 2. የሰው ሃይል፣ የበጀት አቅርቦትና የመረጃ ሥራዎችን ለማከናወን የዝግጅት ሥራዎችን ማከናወን

- የፕላን ኮሚቴ እና የቴክኒክ ቡድን ማደራጀት
- የዝክረ ተግባር ዝግጅት እና በጀት ማስፈቀድ
- የግንዛቤ መድረኮችን ማዘጋጀት

### ተግባር 3. የመሳሪያ ቁሳቁስ ግዢ መፈፀም

- ለገጠር ማዕከላት የሽንሻኖ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስራ የሚውሉ የተለያዩ የቅየሳ መሳሪያዎችን በወቅቱ እንዲገዙ ይደረጋል፡፡

### ተግባር 4. ከማዕከሉ ነዋሪዎች ጋር ዉይይትና የቅኝት ሥራዎችን ማከናወን

- ባለሞያዎች ለቀበሌ አስተዳደሮች እና ለአካባቢው ነዋሪዎች የሚሰሩትን ስራ አይነትና አላማ በግልፅ ያስረዳሉ፣
- ባለሞያዎች የመሬት ላይ የቅኝት ሥራ ያከናውናሉ፡፡

## ለ) የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ምዕራፍ

**ተግባር 1. መረጃ ማሰባሰብ እና መተንተን**

- የተፈጥሮ ገፅታዎችን (ፊዚካል) መረጃዎችን ማሰባሰብ
- ማህበራዊ መረጃዎችን መሰብሰብ
- ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን መሰብሰብ
- የገጠር ማዕከሉን ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር የሚያስተሳስሩ ተቋማት እና መሠረተ ልማቶች መረጃ መሰብሰብ

**ተግባር 2. ከተደራጁት መረጃዎች በመነሳት ለሽንሻኖ ስራ አስፈላጊ የሆኑ የመሬት አጠቃቀሞችን መለየት**

**ተግባር 3. ከተደራጁት መረጃዎች በመነሳት የንድፍ መሠረታዊ ካርታ በተለያዩ አማራጮች ማዘጋጀት**

**ተግባር 4. የሽንሻኖ ሥራ ለማከናወን የቅየሳ ሥራ መሥራት**

- የትራቨርስ ነጥቦችን በትክክል መዘርጋት
- የፖሊጎን ድንጋይ መትከል

**ተግባር 5. የለቀማ እና የስኬች ሥራዎችን መሥራት**

- ይህ ተግባር የስኬች ሥራ በለቀማ ከተሰራ በኋላ በወረቀት ፕሎት ተደርጎ መለስተኛ የሽንሻኖ ሥራ ከተሠራ በኋላ ወደ መሬት ማስተላለፍን ያካትታል፡፡

**ተግባር 6. የተሰበሰበውን መረጃ በወረቀት መቀየር/plotting/**

**ተግባር 7. ፕሎት የተደረገውን ወደዋናው ወረቀት መገልበጥ/Tracing/**

**ተግባር 8. የወረቀቱን ንድፍ ወደ መሬት ማስተላለፍ/Setting out/**

**ተግባር 9. መንገድ የመክፈት ሥራ ማከናወን**

- ዋና መንገድ ስፋት -፤ 20ሜ - 30ሜ
- መጋቢ መንገዶች ስፋት፤ 10ሜ - 15ሜ

**ተግባር 10. ለተለያዩ ዓላማዎች የሚውሉ ብሎኮች (ከ50ሜ-60ሜ) በሚደርስ ስፋት መለየትና ምደባ የመስጠት ሥራ ማከናወን**

**ተግባር 11. የአፈፃፀም ስራዎችን ማከናወን**

- የቀበሌ አስተዳደሩ የሽንሻኖ ፕላኑን መሠረት በማድረግ በግልፅ መመዘኛ መስፈርቶች አዳዲስ የቦታ ጥያቄን ተቀብሎ ያስተናግዳል
- በአፈፃፀም ወቅት የሚጋጥሙ ችግሮች ካሉ ከዞኑ ከሚመለከተው የሥራ ሂደቶች ጋር በመመካከር የማሻሻያ ሥራዎችን ማከናወን፡፡

**ተግባር 12. የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ ማድረግ**

**ተግባር 13. የክትትል ሥራ ማከናወን**

**ተግባር 14. አባሪ ሪፖርት ዝግጅት**

የሽንሻኖ ፕላኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የስራውን ሂደትና በሽንሻኖ ፕላኑ የተከናወኑ ተግባራት ሁኔታ የሚተነትን አጭር የፁሑፍ ሪፖርት ይዘጋጃል፡፡

**ሐ) የፕላን ማስጸደቅ፣ የትግበራ ክትትልና ግምገማ ስራዎች**

የክልሉ የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን የሚጸድቀው በክልሉ የፕላን ተቋም ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በወረዳውና በቀበሌ አስተዳደሩ በጋራ መድረክ ይፀድቃል፡፡ የፕላኑ አስተግባሪ እንደዚሁም ክትትልና ግምገማ የሚከናወነው በክልሉ አካባቢ ጥበቃ በኩል ቢሆንም ለስራው ቅልጥፍና ግን በዞኑ እና በወረዳው የመሬት አስተዳደርና የአካባቢ ጥበቃ የስራ ሂደት በኩል ቢከናወን የተሻለ መሆኑን ለጥያቄዎቻችን ምላሽ የሰጡን የስራ ሃላፊዎችና ባለሞያዎች ጠቁመዋል፡፡

**መ) የቡራኔስት ሞዴል የገጠር የልማት ማዕከል ተሞክሮ**

ቡራ በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ ከባህርዳር በ71 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ የገጠር ቀበሌ ማእከል ነች፡፡ ለገጠር ማእከሉ ፕላን ለማዘጋጀት እየተሰራ ያለው ፕሮጀክት ከስዊዘርላንድ እና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በተውጣጡና በከተማ

ፕላን ዝግጅትና ልማት መስክ በበጎ ፈቃድ በሚሰሩ የባለሞያዎች ቡድን (NEST GROUPS) ጋር በመተባበር የሚሰራ ሲሆን 2002 ዓ.ም ስራው ሊጀመር ችሎአል።

ቡራ የቀበሌው ስም ሲሆን NEST የሚለው የእንግሊዘኛ ምህፃረቃል ደግሞ (New Ethiopian Sustainable Town) የሚለውን ትርጉም የያዘ ነው። የፕሮጀክቱ ዋናው አላማ በክልሉ የገጠር አካባቢዎች የሚቆረቆሩ ጥንስስ ከተሞች እድገታቸው ዘላቂ ከተማ ልማት መርህን የተከተሉና ባላቸው ሃብት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ማመላከት ነው። በፕሮጀክት ጥናቱ መሰረት የአዲሲቷን ሞዴል ከተማ ፕላን በዋናነት በአራት መሰረታዊ ክፍሎች በመክፈል ማለትም 4E የሚላቸው (Ecology, Energy, Education and Exchange) ለእያንዳንዱ የፕላን ክፍል የተግባር ቀጠና አድርጎና እንዴት መስራት እንደሚቻል ያስቀምጣል።

የቡራ የገጠር ማዕከል የፕላን ዝግጅት የሚከተሉትን ዋናዋና የፕላን ዝግጅት ሂደቶችን ያቀፈ ነው።

- ቅድመ ዝግጅት
- ራዕይ ማስቀመጥ
- መረጃ ማሰባሰብና መተንተን
- ፕላን ማዘጋጀት
- ስልጠና መስጠት
- መተግበር

በፕላን ዝግጅት የተሰበሰቡት ዋናዋና መረጃዎች

- የተፈጥሮ ሀብትና የተፈጥሮ አደጋዎች
- ሰብዓዊ መረጃዎችና የሰው መሰረታዊ ፍላጎቶች

በፕላን ዝግጅቱ የተካተቱ ዋናዋና የመሬት አጠቃቀሞች

- የተፈጥሮ ደን ሽፋን
- መኖሪያ እና የመኖሪያ አካባቢ ግብርና
- ማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት
- መንገድ

- ሌሎች መሠረተ ልማቶች

ዋናዋና የፕላን ዝግጅት ሂደቶች

- መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት
- የመሬት አጠቃቀም ፕላን ማዘጋጀት

### 2.3.3. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ

በትግራይ ክልል የሚዘጋጀው የፕላን ዓይነት ገቢራዊ ፕላን (Action plan) ሲሆን የሚከተሉት ዋናዋና የፕላን ዝግጅት ምዕራፎች/phases አሉት፡፡

- የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ማከናወን
- ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ መረጃዎችን በመሬት ላይ ቅየሳና እና በተለያዩ ዘዴዎች ማሰባሰብ
- መሰረታዊ ካርታ ማዘጋጀት
- የፕላን ዝግጅት ማከናወን
- የፕላን ትግበራ ማከናወን

#### ሀ) የቅድመ ዝግጅት ስራዎች

#### ተግባር 1. የፕላን ዝግጅት ሃሳብ ማመንጨት

በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት 193 የሚሆኑ የገጠር የልማት ማዕከላት ይገኛሉ፡፡ ለእነዚህ የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን የሚዘጋጀው በወረዳውና በልማት ማዕከሉ በኩል የፕላን ዝግጅት ጥያቄ ለክልሉ ሲቀርብ በክልሉ የፕላን ዝግጅት የስራ ሂደት በኩል ለአምስት አመት የፕላን ዘመን ያለው ገቢራዊ ፕላን (Action plan) ይዘጋጃል፡፡

**ተግባር 2. የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት ውሳኔ መስጠት**

**ተግባር 3. የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት ዝክረ ተግባር ማዘጋጀትና በጀት ማስፈቀድ**

**ተግባር 4. የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት የቴክኒካል ቡድን እና አስተዳደራዊ ኮሚቴ ማቋቋም**

**ተግባር 5. የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት የትውውቅ ሥራ ማከናወን**

**ለ) የፕላን ዝግጅት ስራዎች**

**ተግባር 1. መረጃ ማሰባሰብ**

- ተፈጥሮአዊ እና ማህበራዊ መረጃዎች በመሬት ላይ ቅየሳና በተያዩ ዘዴዎች መሰብሰብ
- የገጠር ማዕከሉ ከሌሎች የገጠር ማዕከላት ስላለው የመሰረተ ልማት፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር

**ተግባር 2. መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት**

- በመሬት ላይ ቅየሳና በተለያዩ ዘዴዎች በተሰበሰቡ ተፈጥሮአዊ እና ማህበራዊ መረጃዎች በመመስረት መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት

**ተግባር 3. መሠረታዊ ካርታ ተከትሎ የመሬት አጠቃቀም ፕላን ማዘጋጀት ዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች፤**

- መኖሪያና የመኖሪያ አካባቢ ግብርና
- ማህበራዊ አገልግሎቶች
- ንግድ
- የአረንጓዴ ቦታ
- መንገድ

- መዝናኛ እና የአምልኮ ቦታዎች

❖ ክልሉ እየተጠቀመበት ያለውየገጠር ማዕከላት የፕላን ዝግጅት መስፈርት፣ የብሎክ ስፋት እና የመንገድ ስፋት፡

- መስፈርት 1፡5000
- የብሎክ ስፋት እና ርዝመት
    - ➢ ስፋት ከ 40 ሜ - 50 ሜ
    - ➢ ርዝመት ከ 100 ሜ - 120 ሜ
- የመንገድ ስፋት
    - ➢ ዋና መንገድ 20 - 30 ሜ
    - ➢ መጋቢ መንገድ 10 - 18 ሜ
    - ➢ የውስጥ ለውስጥ መንገድ 5- 12 ሜ

❖ በክልሉ በፕላን ዝግጅት ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች

- የገጠር ማዕከሉ የጎግል ኤርዝ ምስል
- የቅየሳ መሳሪያዎች ቶታል ስቴሽን ወይም(ጂፒኤስ፣እና የመሳሰሉት)
- ኮምፒውተር፣ የኮምፒውተር ሶፍት ዌሮች( አውቶ ካድ፣ መሰረታዊ ኮምፒውተር)

## ሐ) የፕላን ማስጸደቅ፣ ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ስራዎች

### ተግባር 1. የገጠር የልማት ማዕከሏን ፕላን ማሰፀደቅ

- የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ትክክለኛነት በክልሉ የፕላን ተቋም ከተረጋገጠ በኋላ በወረዳውና በገጠር ማዕከሉ አስተዳደር ይፀድቃል፡፡

## ተግባር 2. ፕላኑን ወደ መሬት ማውረድ

- ፕላኑን መሠረት በማድረግ የመሬት ላይ ቅየሳ ማድረግ
- የማዕዘን ድንጋዮች መትከል እና የሽንሻኖ ስራ ማከናወን
- የመንገድ ከፈታ ማከናወን

## ተግባር 3. ክትትልና ግምገማ ማድረግ

- የፕላኖቹ ክትትልና ግምገማ የሚከናወነው በክልሉ የከተሞች ፕላን ሬትላተሪ የሥራ ሂደት ነው፡፡
- የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን በተመለከተ በአመት አንድ ጊዜ ፕላኑን ከመሬት ጋር በማገናዘብ የግምገማውን ውጤቱ ግብረመልስ ለወረዳው አስተዳደር መስጠት

## 2.3.4. የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ

በደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር የልማት ማዕከላት ወደፊት ሊሰራ የታቀደው የፕላን ዓይነት ስኬች ፕላን ነው፡፡ የፕላን ዝግጅቱ እንዲከናወን የታቀደው ለልዩ ወረዳዎች በክልሉ የከተማ ፕላን የሥራ ሂደት በኩል ሲሆን፤ በዞን መዋቅር ውስጥ ላሉ የገጠር የልማት ማዕከላት ደግሞ በክልሉ የከተማ ፕላን የስራ ሂደት የቴክኒክ ድጋፍ እየተደረገ ፕላኑ የሚዘጋጀው በዞን የፕላን የሥራ ሂደት በኩል ነው፡፡

የፕላን ዝግጅቱ የሚከተሉት ዋናዋና የፕላን ዝግጅት ሂደቶች እንዲኖሩት ታስቧል፡፡

- የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች
- የገጠር ማዕከሉን የመሬት ላይ ቅየሳ ማድረግ
- መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት
- ስኬች ፕላን ማዘጋጀት
- ፕላን ማፅደቅ እና መተግበር
- የክትትልና ግምገማ ሥራ ማከናወን

## ሀ) የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ

### ተግባር 1. የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት የመነሻ ሃሳብ ማቅረብ

- ለገጠር የልማት ማዕከላት ለሚዘጋጀው ፕላን የመነሻ ሃሳብ የሚነሳው በወረዳውና በገጠር ማዕከላት አስተዳደር ሲሆን ጥያቄው ለክልል የፕላን ተቋም የሚቀርበውም በዞን የከተሞች አደረጃጀት የሥራ ሂደት በኩል ነው፡፡

### ተግባር 2. የፕላን ዝግጅት ጥያቄ ማፅደቅ፣

### ተግባር 3. ለፕላን ዝግጅቱ አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ፣

- የፕላን ዝግጅቱን በተሟላ መልኩ ለማደራጀትና ለመምራት የሚያስችል ዝክረ ተግባር በማዘጋጀት አስፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ

### ተግባር 4. የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት አስተዳደራዊና ቴክኒካል ቡደን ማቋቋም

- ከወረዳና ከቀበሌው የልማት ማዕከል የፕላን ዝግጅቱ የበላይ አስተባባሪ ማቋቋም
- የፕላን ዝግጅቱ የቴክኒክ ቡድን አንድ የከተማ ፕላነር እና ሁለት የቀየሳ ባለሞያዎችን ባቀፈ መልኩ ማደራጀት

### ተግባር 5. የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ማከናወን

- በወረዳው መስተዳድር በኩል መድረኮችን በማመቻቸት ከገጠር ማዕከላት ነዋሪዎችና ከዋናዋና የባለድርሻ አካላት ጋር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ማከናወን፡፡

## ለ) የፕላን ዝግጅት ስራዎች

### ተግባር 1. መረጃዎችን ማሰባሰብ

- የገጠር ማዕከሏ ተፈጥሮአዊ ገፅታ መረጃዎችን ማሰባሰብ
- የመሰረተ ልማት አቅርቦት መረጃዎችን ማሰባሰብ
- የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት
- ዋናዋና የመሬት አጠቃቀም መረጃዎችን
- የህዝብ ብዛት

### ተግባር 2. መሰረታዊ ካርታ ማዘጋጀት

- በመሬት ላይ ቅየሳ ወይም ሳተላይት ስቴሪዮ ምስል በተሰበሰበው መረጃ መሰረት መሠረታዊ ካርታ ማዘጋጀት

### ተግባር 3. ፕላን ማዘጋጀት

- መሠረታዊ ካርታን ተከትሎ  የገጠር ማዕከሏን መነሻ  የፕላን ንድፍ ማዘጋጀት
- በዚህ መነሻ  የፕላን ንድፍ መሠረት ዋናውን ፕላን መቅረፅ

በፕላን ዝግጅቱ የሚካተቱ ዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች፡

- መኖሪያና የመኖሪያ አካባቢ እርሻ
- ንግድ
- የማህበራዊ አገልግሎቶች
- የጎጆ ኢንዱስትሪዎች
- የአረንጓዴ ቦታዎች
- ስፖርትና መዝናኛ አስተዳደራዊ ተቋማት መሆናቸውን ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

የመሬት አጠቃቀሙ ፕላን የሚዘጋጀው እንደ ማዕከሏ ስፋት ተጨባጭ ሁኔታ በ1፡5000 ወይም በ1፡2000 መስፈርት ሲሆን የዋናው መንገድ ስፋት 30 ሜትር ነው።

የብሎክ መጠኑ ደግሞ፡

- ርዝመት - 120 ሜ - 150 ሜ
- ስፋት - ከ30 ሜ - 50 ሜ

## ሐ) የፕላን ማስጸደቅ፣ ትግበራ እና ክትትልና ግምገማ ስራዎች

### ተግባር 1. ፕላን ማፅደቅ

- በክልሉ የከተሞች አደረጃጀት ፕላን ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ በወረዳውና በገጠር ማዕከሏ አስተዳደር ይፀድቃል።

### ተግባር 2. ፕላን መተግበር

የፕላኑ አስተግባሪ  የገጠር ማዕከሉ የሚገኝበት የዞን ከተማ ልማት መምሪያ እና የወረዳው አስተዳደር በመሆናቸው በትግበራ ምዕራፍ የሚከተሉት ዋናዋና ተግባራት ይከናወናሉ።

- በወረዳው መዋቅር የፕላን የሥራ ክፍል በመፍጠር መረጃዎችን ማኖር
- ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማመቻቸት
- የመሬት ላይ ቅየሳ በማድረግ የማዕዘን ድንጋዮችን መትከል
- የመንገድ ከፈታ ማከናወን
- የመሬት አቅርቦትና የመሬት ልማት ማከናወን

### ተግባር 3. የክትልና ግምገማ ስራ ማከናወን

- በዞን ከተማ ልማት መምሪያዎችና በወረዳ አስተዳደሮች በኩል የፕላኖቹ ክትትልና ግምገማ ይከናወናል፡፡
- ከዞኑ አቅም በላይ ለሆኑ ጉዳዮች ወደ ክልል ይመራል፡፡

## 2.3.5. ከክልሎች የተገኙ ጠቃሚ ልምዶች

ሀ) ፕላን የሚዘጋጅላችው የገጠር ማዕከላት ምርጫ ሲወሰን በተለያዩ መመዘኛ መስፈርቶች መሆኑ እና ከነዚህም መስፈርቶች ጥቂቶቹ ለወደፊቱ የከተማነት መስፋፊያነት አመቺ መሆን፣ አፈሩ ለግንባታ የማያስቸግር መሆን፣ ውኃ በአቅራቢያው በቀላሉ ሊገኝበት የሚችል መሆን፣ የተዳፋት መጠኑ ከ2-16% ያልበለጠ መሆኑ፣

ለ) የገጠር ማዕከላት ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ በየደረጃው ያሉትን የመንግስት እና የህብረተሰብ ክፍል ባሳተፈ መልኩ መመራት ያለበት መሆኑ፣

ሐ) የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን የቅየሳ ባለሙያ፣የከተማ ፕላነር፣ የሚያስፈልጉት መሆኑ፣

መ) የገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት የመሬት ቅየሳ በተሰበሰበ የተፈጥሮ ገፅታ መረጃዎች ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት፣

ሠ) በፕላን ዝግጅት ወቅት የሚሰበሰበው መረጃ የገጠር ማዕከሉ ከአጎራባች የገጠር ማዕከላት ጋር ያለው አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስር መረጃ የሚሰበሰብ መሆኑ፣

ረ) የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ወሰን የሚወሰነው ቴክኒካዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት በወረዳው እና በገጠር ማዕከላት ፕላን ኮሚቴዎች በመስማማት መሆኑ፣

ሰ) በገጠር ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ውስጥ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የመሬት አጠቃቀም በፕላን ውስጥ የሚካተቱ መሆናቸው፣

ሸ) በፕላን ዝግጅት ወቅት ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ምድቦች የመኖሪያ፣ የንግድ፣ የአገልግሎት፣ የአስተዳደር፣ መዝናኛ እና የመሳሰሉት የሚካተቱ መሆናቸው፡፡

ቀ) የልማት ማዕከላት የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ሂደቱ በአጠቃላይ እስከ 90 ቀናት ያህል ይፈጃል ተብሎ የሚገመት መሆኑ፣

በ) የፕላን አተገባበር ክትትልና ግምገማ የሚከናወነው በዋናነት በክልሉ የከተሞች ልማት/ፕላን ኢኒስቲቲት/ ቢሮ በኩል እና በዞኑ የፕላን የሥራ ሂደት በኩል መሆኑ፣

ተ) በክልሎች ለገጠር የልማት ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ሲዘጋጅ የመንገድ ስፋት አንደኛ መንገድ ከ20 - 30 ሜ፣ ሁለተኛ መጋቢ መንገዶች 10-18 ሜ እና የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ስፋት 5 - 12 ሜ መሆኑ፣

ቸ) የብሎክ መጠን ርዝመት 120ሜ - 150ሜ እና ስፋት 30ሜ - 50ሜ መሆኑ፣

ኘ) በገጠር ማዕከላት የመሬት አጠቃቀም ፕላን ላይ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል የመሬት መጠን በመቶኛ ድርሻ ተሰልቶ የሚሰጥ መሆኑ በዋነኛነት ተጠቃሽ ናቸው፣

## 2.4 .የገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን ዝግጅት መሰረታዊ መርሆዎች

የገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን በሚዘጋጅበት ወቅት ፕላኑን የሚያዘጋጀው ቡድን ወይም በስራው ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ስራቸውን ማከናወን ያለባቸው የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎችን መሰረት ባደረገ መንገድ መሆን አለበት፡-

- በገጠር የልማት ማዕከላት ለግንባታ የሚውለው ቦታ ለም የእርሻ መሬትን የሚሻማ እንዳይሆን፣
- በአፈር ባህሪው ለግንባታ ምቹ፣ ድንጋያማ፣ የመሬት መንሸራተት የሌለበት እና ለውሃ አቅርቦት ምቹ አካባቢ መሆን እንዳለበት፡፡
- የገጠር ማዕከላት በአብዛኛው በግብርና የሚተዳደሩ ነዋሪዎች የሚኖሩበት መሆኑና በቅርብ ርቀት ላሉ ከተሞች የግብርና ምርቶችን ለማቅረብ ባለሃብቶች ሊሳቡ
- ስለሚችሉ በቂ የከተማ ግብርና (Urban Agriculture) ቦታዎች ሊዘጋጁላቸው እንደሚገባው፡፡
- የሚሰራው የስኬች ፕላን ስራ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ መሆን አለበት፤
- ስራው በዋናነት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸው ችግሮችን በመፍታት ላይ ማተኮር አለበት፤
- የሚሰራው የስኬች ፕላን ሌሎች በአካባቢው ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ ወይም ወደፊት ሊሰሩ የታሰቡ የእድገትና የልማት እቅዶችን ለመተግበር የሚያግዝ መሆን አለበት፤
- የመሬት አጠቃቀም ፕላኑ ቅይጥ የመሬት አጠቃቀምን የሚያበረታታ መሆን አለበት
- በስኬች ፕላን ዝግጅትና ትግበራ የነዋሪውና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መረጋገጥ አለበት
- እርስ በርስ የማይጣጣሙ የመሬት አጠቃቀሞችን በመነጣጠል በማዕከሉ በተለያዩ ቦታዎች እንዲለሙ መመደብ አለበት፤
- ብክለትን ለማስከተል እምቅ ሃይል ያላቸውን ለምሳሌ ከፍተኛ ድምፅ፣ ሽታ፣ ብርሃን፣ ጫና ያለባቸውን መንገዶችን እና የኢንዱስትሪ ቦታዎችን ለይቶ ማዬት፤
- ለህብረተሰቡ ዕለት ተዕለት አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማእከል አካባቢ እንዲሆኑ ማድረግ፤

- ዋና ዋና ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን በማዕከል ወይም አመቺ በሆኑ ሥፍራዎች መመደብ፤
- ለዋና ዋና ህዝባዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በአዲስ አካባቢ እንዲለሙ ከማድረግ ይልቅ ባሉበት ቦታ መልማት እንዲቀጥሉ እድል መስጠት ናቸው፡፡

የመሬት አጠቃቀም ፕላን መርሆዎች የወደፊት የመሬት አጠቃቀም ካርታ ዝግጅትን አቅጣጫ በመምራት ሊያግዙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ጠቅላላ መርሆች በተለያዩ ምድቦች የተከፋፈሉ ሲሆኑ እንደ አከባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ሌሎች የመሬት አጠቃቀሞችን ሊያካተቱ ይችላሉ፡፡

## 2.5. የገጠር የልማት ማዕከላት የስኬች ፕላን ዝግጅት ምዕራፎች/Phases/

የመሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅት የተሻለ ጥራት የሚኖረው በቅደም ተከተል በተደራጁ በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ አልፎ ሲጠናቀቅ መሆኑን የተለያዩ ሃገራት የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ ተሞክሮ ያሳያል፡፡

በሃገራችንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ከተማነት ይለወጣሉ ተብለው ለሚገመቱ የገጠር ማዕከላት ፕላን ዝግጅት እና ትግበራ በሚከተሉት ምእራፎች አልፎ ቢጠናቀቅ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡-

ምዕራፍ/Phase/ 1. የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ

ምዕራፍ/Phase/ 2. መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማደራጀት

ምዕራፍ/Phase/ 3. መረጃዎችን ማጠናቀር እና መተንተን

ምዕራፍ/Phase/ 4. የስኬች ፕላኑ ፅንሰሃሳብ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

ምዕራፍ/Phase/ 5. ዋናውን የስኬች ፕላን ማዕቀፍ ማዘጋጀት

ምዕራፍ/Phase/ 6. ፕላኑን ማፀደቅ

ምዕራፍ/Phase/ 7. ፕላኑን መተግበር፣ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ

### 2.5.1 ምዕራፍ/Phase/ 1. የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ

#### ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት የገጠር ማዕከሏን ነባራዊ ሁኔታ በመዳሰስ የመነሻ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለፕላን ስራዉ መነሻ ሃሳብ ለመቅረፅ የሚያግዙ ቅድመ ዝግጅት ተግባራት እና ዝርዝር ተግባራትን በመጠቆም እና የፕላን ዝግጅቱ ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊውን ሀብት በመዘርዘርና በማጠቃለያው የሚጠበቀውን ውጤት ለማስቀመጥ ነው፡፡

#### ለ) ዋናዋና ተግባራት

**ተግባር** 1.ፕላን ለመስራት መነሳሳት
**ተግባር** 2. የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ
**ተግባር** 3. የገጠር ማዕከሏ የፕላን ዝግጅት ጥያቄን ማፅደቅ
**ተግባር** 4. ፕላኑን ለመስራት እቅድ ማውጣት
**ተግባር** 5. ዝክረ - ተግባር ማዘጋጀት

#### ሐ) የሚጠበቅ ውጤት

- በፕላን ዝግጅት ዙሪያ የፀደቀ ውሳኔ
- የተዘጋጀ ዝክረ ተግባር
- የፕላን ስራዉን የሚመራ እና የሚቆጣጠርና የበላይ ጠባቂ ኮሚቴ እና የቴክኒክ ቡድን ማዋቀር
- የባለድርሻ አካላትን ያቀፈ የምክክር መድረክ ማቋቋም
- የተጠናቀረ ሪፖርት
- የስምምነት ሰነድ መፈራረም

## መ) ሃላፊነት የተሰጠው አካል

የገጠር ማዕከላት የፕላን ዝግጅት ጥያቄ ለክልሉ የፕላን ተቋም በወረዳው ምክር ቤት ወይም በዞኑ የከተማ ልማት የሥራ ሂደት በኩል ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ስራውን በሃላፊነት የመምራትና ኮሚቴዎችን የማዋቀር ድርሻ ግን እንደክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም በአመዛኙ ሀላፊነቱ የሚወድቀው በዞኑ በሚገኘው የከተማ ልማት የሥራ ሂደት እና በወረዳው ምክር ቤት ላይ ነው፡፡ ፕላኑን ለመስራት እቅድ ማውጣትና እና ዝክረ ተግባር ለማዘጋጀት ሃላፊነት የሚሰጠው በዋናነት ለወረዳው ምክር ቤት እና ፕላኑን ለሚሰራው የቴክኒክ ቡድን ሲሆን ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ይሆናል፡፡

## ሠ) ለሥራው የሚያስፈልገው ሰዓት - 15 - 20 ቀን

## ረ) መነሳት የሚገባቸው ቁልፍ ጥያቄዎች

- የፕላን ዝግጅት የሚመራ ኮሚቴ ተደራጅቷል?
- የተደረገው የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ለገጠር ማዕከሉ ፕላን መዘጋጀት እንዳለበት ያሳያል?
- በባለድርሻ አካላት መካከል የተደረገው ውይይትና ድርድር ለገጠር ማዕከሉ ፕላን መዘጋጀት እንዳለበት መስማማታቸውንና ለስራውም ተባባሪ መሆናቸውን ያሳያል?
- በመነሻ ሃሳቡ መሰረት ፕላን ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ተለይተዋል ?
- የተሰበሰበው መረጃ በቂ ነው?
- የስራው ሂደት አሳታፊ ነበር?
- የፕላን ስራው ውስጥ የሚካተቱ ጉዳዮችና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች በሚገባ ተለይተዋል?
- ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች የተለዩት በአካባቢው ነዋሪዎች ነውን?
- በአካባቢው ያለው ነባራዊ ሁኔታ በሚገባ ተተንትኖአል?

## ሰ) ዝርዝር ተግባራት

### ተግባር 1.ፕላን ለመስራት መነሳሳት

የዚህ ተግባር ዓላማ በአካባቢው ያለው ነዋሪ፣ የወረዳው ምክር ቤት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ለገጠር የልማት ማዕከሉ ፕላን ዝግጅት ጥያቄ የሚያነሱበትን ሂደት ማሳየት ነው።

- የገጠር ቀበሌ ማዕከሉ አስተዳደርና የወረዳው ምክር ቤት በፕላን ዝግጅት አስፈላጊነት ከዞን የፕላን ተቋማት ጋር የመነሻ ውይይት ማድረግ እና መስማማት።
- የተለያዩ ስብሰባዎችን በማዘጋጀትና ነዋሪዎችን ስለ ፕላን አስፈላጊነት ግንዛቤ ማስጨበጥ
- በፕላን ስራው ውስጥ ተሳትፎ ለሚያደርጉ ግለሰቦችና ባለድርሻ አካላት ማስታወሻ በመላክ ማሳወቅ፤
- ለባለድርሻ አካላት ሰፊ ገለፃ በማድረግ ስለ ፕላን ዝግጅቱ አስፈላጊነት በማስረዳት የጋራ ግንዛቤ ማስያዝ፤

### ተግባር 2. የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ

- የአካባቢው ነዋሪና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ፍላጎትን በተመለከተ መረጃ በመሰብሰብና በዝርዝር በማጥናት ብሎም ማጠቃለያ በመስራት ውጤቱን ለክልሉ ለከተማ ፕላን ተቋም ይፋ ማድረግ።

### ተግባር 3. የገጠር ማዕከሏ የፕላን ዝግጅት ጥያቄን ማፅደቅ

ፕላን የሚዘጋጅላቸው የገጠር ማዕከላት ምርጫ መስፈርቶች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም የሚከተሉት ዋና ዋናዎች ናቸው።

- ወደፊት ለከተማ ማስፋፊያነት አመቺ መሆኑ(የመሬት አቀማመጥ፣ የአፈሩ ዓይነት፣በቂ የውሃ አቅርቦት መኖሩ..)
- የቀበሌ ማዕከሉ የህዝብ ድጋፍ
- የቤቶች እና የህዝብ ቁጥር ብዛት
- የወረዳው አስተዳደር ድጋፍ
- በገጠር ማዕከሉ ያለው የሥራ ዓይነት ስብጥር
- በቀበሌ ውስጥ ያሉ የአስተዳደርና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ማዕከልነት
- የገጠር ማዕከሉ የገበያ ማዕከልነት
- የገጠር- ገጠር እና የገጠር - ከተማ ትስስር አመቺነት

## ተግባር 4. ፕላኑን ለመስራት እቅድ ማውጣት

የዚህ ተግባር ዋናው ዓላማ የገጠር ማዕከሏ የፕላን ዝግጅት አስፈላጊነት በዞን እና/ወይም/ በክልሉ መስተዳድር የሚመለከተው አካል ይሁንታ ከተገኘ በኂላ ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን መሰብሰብና ማቀናጀት ብሎም ስራውን በበላይነት የሚመራና የሚቆጣጠር አካል በማደራጀት ለፕላን ሥራው ዕቅድ ማውጣት ነው፡፡ ይህም ተግባር በወረዳው አሰተዳደርና በዞኑ የፕላን ተቋም በኩል የሚከናወን ይሆናል፡፡

የፕላን ስራውን ከመጀመርያው ጀምሮ የሚከታተልና የሚቆጣጠር ከተቻለም ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጥ ኮሚቴ ከነዋሪዎች፣ ከገጠር ማዕከሉ አስተዳደር፣ ከወረዳው አሰተዳደር፣ ከዞን የፕላን የሥራ ሂደት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ማዋቀር እና የፕላኑን ዝግጅት ስራውን የሚያከናውነውን እና የሚከታተል ቡድን ወይም ተቋም በማዋቀር በተቻለ መጠን ስራው ሁሉንም ያሳተፈና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሁም በተያዘለት ጊዜ የሚጠናቀቅ እንዲሆን ለማስቻል ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡

## ተግባር 5. ዝክረ - ተግባር ማዘጋጀት

- ዝክረ ተግባሩ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን ዋናዋና ይዘቶች ሊያካትት ይገባል
  - መግቢያ
  - መነሻ ሃሳብ
  - ፅንሰሃሳባዊ የፕላን ማእቀፍ
  - ራእይ፣ ግብ እና ዓላማ
  - የፕላን ዝግጅት ሂደትና ዘዴው
  - የስራው ወሰን
  - የሚጠበቁ ውጤቶች
  - ዋና እና ዝርዝር ተግባራት
  - አስፈላጊው የሃብት ወይም የግብአት አቅርቦት
  - የሥራው ሪፖርት አቀራረብ
  - የሥራው ድርጊት መርሃ-ግብር
- ዝክረ ተግባሩን ማፅደቅ እና አሰፈላጊውን በጀት ማስፈቀድ
- ለስራው አስፈላጊ የሆነውን ሃይል ማደራጀት እና መመደብ
  - የፕላን ዝግጅት የቡድን መሪ መመደብ
  - ሌሎችን የቡዱኑን አባላት መምረጥ
  - ለቡዱኑ አባላት ዝክረ ተግባሩን መስጠት
  - የትብብር ደብዳቤ ለሚመለከታቸው አካላት መፃፍ
  - ለሥራው አሰፈላጊ የሆነውን ግብዓት ወጪ ማድርግ
  - የፕላን ቡድን አባላትን ማሰማራት

❖ **ማስታወሻ** - የፕላን ቡድኑን አባላት የሙያ ሥብጥር በክፍል ሦስት ይመልከቱ

## 2.5.2. ምዕራፍ/ Phase/ 2. መረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማደራጀት

### ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት የገጠር የልማት ማዕከሏን መሠረታዊ ካርታ ዝግጅት የሚያግዝ በመሬት ላይ እና በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የገጠር ማዕከሉን የተፈጥሮ ገፅታ፣ እና ሰው ሠራሽ ሁኔታዎች በተመለከተ መረጃዎችን በመሰብሰብ የገጠር ማዕከሉን የመሰረታዊ ካርታ ማዘጋጀት ነው፡፡ ይህ ደረጃ ሙያዊ የፕላን ዝግጅት ሥራ የሚጀምርበት ክፍል ነው፡፡ መረጃ መሰብሰብ ከመጀመሩ በፊት የሚሰበሰበው የመረጃ ዓይነት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን እና የመረጃ ምንጮችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከሚጠበቁ የፕላን ዝግጅት ግብ እና ዓላማ ጋር የተዋሃዱ መሆን አለባቸው፡፡

### ለ) ዋናዋና ተግባራት

**ተግባር 1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መወሰን እና መቅረፅ**

**ተግባር 2. መረጃዎችን መሰብሰብ**

**ተግባር 3. የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማደራጀት**

**ተግባር 4. መሠረታዊ ካርታ (Base map) ማዘጋጀት**

### ሐ) የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች እና የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች
- የተጠረዙ የተሰበሰቡ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ መረጃዎች
- መሠረታዊ ካርታ (Base map)
- ሪፖርቶች

**መ)ሃላፊነት የተሰጠው አካል**

- የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን

**ሠ) ለሥራው የሚያስፈልገው ሰዓት- ከ20-25 ቀን**

**ረ) ቁልፍ የማረጋገጫ ጥያቄዎች**

- የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ናቸው?
- የመረጃ መሰብሰቢያ ቅፆች ግልፅ ሆነው የተዘጋጁ ናቸውን?
- የተሰበሰቡ መረጃዎች ፕላኑን ለመስራት ሁሉንም የሚያጠቃልሉ ናቸውን?

**ሰ) ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መወሰን እና መቅረፅ**

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን ዓይነት ለመወሰን እና ለመቅረፅ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፤

- **የሚሰበሰቡት የመረጃ አይነቶችን እና ምንጫቸውን መለየት**
  - የገጠር ማዕከሏን ዋና ዋና ችግሮች እና መለያዎች ከዝክረ-ተግባሩ መለየት
  - በፕላን ዝግጅቱ የሚተኮሩባቸውን ዋና ዋና የፕላን ክፍሎችን መዘርዘር
  - ዝክረ ተግባሩን በመዳሰስ ተፈላጊ የሆኑ የመረጃ ዓይነቶችን መለየት
  - ለተፈላጊ የመረጃ ዓይነቶች ዋና ዋና የመረጃ ምንጮችን መለየት

- **የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እና መሳሪያዎችን መወሰን**

የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚከተሉት ዘዴዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡-

- ምልከታ ማድረግ
- የተለያዩ የቅየሳ መሳሪያዎችን መጠቀም
- የሳተላይት ስቴሪዮ ምስል (3D)
- ውይይት ማካሄድ
- በድምፅ እና በምስል መቅረጫዎች መቅረፅ
- የፁሑፍ እና የቃል መጠይቅ ማድረግ

የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚከተሉት ዘዴዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡-

- አስፈላጊ የሆኑ የመረጃ ዓይነቶችን እና ምንጮችን መለየት
- ተዛማጅ ፁሑፎችን መዳሰስ
- ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ከተዛማጅ ፁሑፎች ማሰባሰብ

➢ **የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅፃችን እና መሳሪያዎችን ማዘጋጀት**

- የማረጋገጫ ዝርዝር
- የቃል እና የፅሑፍ መጠይቅ
- የምልከታ ቦታዎችን እና ይዘቶችን መለየት
- የተለያዩ የቅየሳ እና የካርታ መስሪያ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት (ዝርዝሩን በክፍል 3.2. ይመልከቱ)

**ተግባር 2. ስለገጠር ማዕከሉ መረጃዎችን መሰብሰብ**

➢ **የገጠር ማዕከላትን መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የገጠር ማዕከሉን መሠረታዊ ካርታ ለማዘጋጀት በመሆኑ በማዕከሉ እና በአካባቢው የሚገኘውን የመሬት ላይ መረጃ ለማሰባሰብ እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ይቻላል፡፡**

- የመሬት ላይ የቅየሳ መሳሪያዎችን ለምሳሌ ቶታል ስቴሽን ወይም ሌሎች የቅየሳ መሳሪያዎችን በጥምር በመጠቀም ለምሳሌ ቴዶላይት፣ ዲጂታል ጂፒኤስ እና ሌቭሊንግ በመጠቀም
- ከሌሎች ነባር ካርታዎች የሳተላይት ምስል በሚገኙ መረጃዎች
- ሳተላይት የስቴሪዮ (3D) ምስልን በመግዛት
- በአቅራቢያ ካለ ትልቅ ከተማ የተነሳ የአየር ፎቶን በመጠቀም

➢ **በመጀመሪያ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚሰበሰቡ ነባራዊ የመሬት አጠቃቀም መረጃዎች**

**1. ተፈጥሮአዊ የመሬት ገፅታ መረጃዎች**

- የመሬት አቀማመጥ
- የውሃ አካላት
- የደን ሽፋን
- ረግረግማ ቦታዎች
- የጂኦሎጂ የተፈጠሮ አደጋ ያላቸው ቦታዎች ካሉ

**2. ሠውሠራሽ መረጃዎች**

- የመኖሪያ መሬት አጠቃቀም መረጃ
- የመኖሪያ አካባቢ ግብርና መሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለአስተዳደር ሥራ የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለንግድ ሥራ የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለአገልግሎት መስጫ ተቋማት የዋለው የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለትራንስፖርት አገልግሎት የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለስፖርት እና መዝናኛ አገልግሎት የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለእርሻ አገልግሎት የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ
- ለሌሎች አገልግሎቶች የዋለ የመሬት አጠቃቀም መረጃ

➢ **በሁለተኛ የመረጃ ማሰበሰቢያ ዘዴ የሚሰበሰቡ መረጃዎች**

## 1. ተፈጥራዊ መረጃዎች

- ጂኦግራፊያዊ እና አንፃራዊ አቀጣጫ
- የአየር ፀባይ (ዝናብ፣ ሙቀት፣ የንፋስ ሁኔታ..)
- የአፈር ዓይነት

## 2. ሰብዓዊ መረጃዎች

- ሥነ-ህዝብ
- ታሪካዊ እና ባህላዊ መረጃዎች

## 3. በገጠር ማዕከሏ ስላለው የማህበራዊ አገልግሎት

## 4. ከገጠር ማዕከሏ ትስስር ስላላቸው አካባቢዎች መረጃ መሰብሰብ

- ተፈጥሮአዊ እና አካባቢያዊ ትስስር የተመለከተ መረጃ መሰብሰብ
- ስለ መሠረተ ልማት ትስስር
- ስለኢኮኖሚያዊ ትስስር መረጃ መሰብሰብ
- ስለማህበራዊ ትስስር መረጃ መሰብሰብ
- በትስስር ላይ ማነቆ ሊሆኑ ስለሚችሉ ጉዳዮች መረጃ መሰብሰበ

የሚከተለት በአንድ አካባቢ ትስስር ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

- ጂኦግራፊያዊ ቀረቤታ
- የማህበራዊ አገልግሎት አቅርቦት
- የግብርና ምርት ውጤቶች አቅርቦትና የገበያ ትስስር
- በትራንስፖርት ረገድ ያለው ትስስር
- የልማት ፕሮጀክቶች መኖር
- አስተዳደራዊ አገልግሎት መኖር
- የመዝናኛ እና ቱሪዝም አገልግሎት መኖር

**ተግባር 3. የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማደራጀት**

- ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በየርዕሱ እና በየአይነቱ አደራጅቶ ማስቀመጥ
- መረጃዎችን ተራ ቁጥር ሰጥቶ ለቆጠራ/ ለትንታኔ ማዘጋጀት
- በመጠን ወይም በዓይነት የተሰጡትን ምላሾች በሰንጠረዥ ማስቀመጥ
- በሰንጠረዥ የተቀመጡትን መረጃዎችን እንደአስፈላጊነቱ በግራፍ እና በቻርት ማስቀመጥ

**ተግባር.4. ነባራዊ የተፈጥሮ እና የመሬት አቀማመጥ የሚያሳይ መሠረታዊ ካርታ (Base map) ማዘጋጀት**

የገጠር የልማት ማዕከሉን የመሠረታዊ ካርታ ለማዘጋጀት የተለያዩ ዜዴዎችን መጠቀም የሚቻል ሲሆን እነዚህ የተለያዩ ዘዴዎች የሚፈጁት ጊዜ፣ የጥራት እና የወጪ ደረጃቸው በዚያው መጠን የሚለያይ በመሆኑ እና በሀገሪቱ የሚገኙ የገጠር የልማት ማዕከላት ቁጥር ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር የሚከተሉት አነስተኛ ጊዜን እና ወጪን የሚጠይቁ የመሠረታዊ ካርታ ዝግጅት ዘዴዎች በዚህ ማንዋል ውስጥ ተካተዋል።

➢ **ሳተላይት የስቴሪዮ ምስልን በመጠቀም የፎቶግራሜትሪ (photogrammetry) ሂደትን በመከተል የመሠረታዊ ካርታን ማዘጋጀት፡**

ይህ ዘዴ አነስተኛ ጊዜን እና ወጪን የሚጠይቅ ቢሆንም በመሬት ላይ በሚሰበሰብ መረጃ ንፅፅር ካልተደረገ የጥራት ደረጃው ዝቅተኛ ሊሆን የሚችል ሲሆን በሚከተሉት ሂደት ሊዘጋጅ ይችላል።

- የፎቶግራሜትሪ ሀርድ እና ሶፍት ዌር መግዛት
- የገጠር ማዕከሉን ከሳተላይት ስቴሪዮ ምስልን(3D) መግዛት
- (ከኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ድርጅት ጋር ግንኙነት በመፍጠር)

- ሳተላይት ስቴሪዮ ምስልን በመጠቀም ከመሬት ላይ በሚሰበሰብ የመቆጣጠሪያ ነጥቦች መረጃ ተጠቅሞ የኤሪያል ትሪአንጉሌሽን (AT) ማከናወን
- በስሪ ዲ (3D) ቴክኖሎጂ ከተስተካከለው ስቴሪዮ ምስል ላይ በጂ.አይ.ኤስ. መሠረታዊ ካርታ በማዘጋጀት ሂደት መረጃ መውሰድ (Digitalization/ feature extraction)
- የተሰበሰቡ መረጃዎችን ቀደም ብሎ በተዘጋጀ ተመጋጋቢ ዳታ ቤዝ ማደራጀት (ከገላጭ መረጃዎች ጋር ማስተሳሰር)
- ወደ ካርታ ማቀናበር (map composition)

➢ **በምድር የቅየሳ ዘዴ የሚዘጋጅ መሠረታዊ ካርታ**

- ቶታል ስቴሽን በመጠቀም በመሬት ላይ ቅየሳ የተሰበሰበውን መረጃ ማደራጀት
- ቶታል ስቴሽን ከሌለ ሌሎች የቅየሳ መሳሪያዎችን በጥምር መጠቀም (ቴዶላይት፣ ጂፒኤስ፣ ሌቬሊንግ እና የመሳሰሉትን)
- የተሰበሰበውን መረጃ ወደ ጂ.አይ.ኤስ መገልበጥ/displaying/
- በጂ.አይ.ኤስ. መሠረታዊ ካርታ በማዘጋጀት ሂደት መረጃ መውሰድ (Digitalization/ feature extraction)
- የተዘጋጀውን መሠረታዊ ካርታ በ(PDF) ወደዋናው ወረቀት መገልበጥ/printing/

**ማስታወሻ፡** የገጠር የልማት ማዕከላት መሠረታዊ ካርታ በ1፡5000 መስፈርት መዘጋጀት ይኖርበታል

### 2.5.3. ምዕራፍ/ Phase/ 3. መረጃዎችን ማጠናቀር እና መተንተን

**ሀ)** ይህ ምዕራፍ ስለተሰበሰቡ የመሬት አጠቃቀም መረጃዎች ትንታኔ የምንሰጥበት ክፍል ነው፡፡ ትንታኔው ተፈጥሮአዊ፣ የሥነ- ህዝብ፣ ማህበራዊ እና ታሪካዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን የሚያጠቃልል ቢሆንም በአካባቢው ስላለው የመሬት አጠቃቀም ነባራዊ ሁኔታ በመለየት ለወደፊት በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ ከፕላን ቅኝት አንፃር የመፍትሄ ሃሳቦች የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

**ለ) የዚህ ምዕራፍ ዋናዋና ተግባራት**

**ተግባር 1.** ትንታኔ የሚሰጥበትን ዘዴ መለየት

**ተግባር 2.** ትንታኔ የሚሰጥባቸውን ነጥቦች መለየት

**ተግባር 3.** ስለተጠናቀሩት መረጃዎች ትንታኔ እና መግለጫ መስጠት

**ሐ) የሚጠበቁ ውጤቶቸ**

- ተፈጥሮዊ የመሬት ገፅታ፣ ማህበራዊ እና በሌሎች ጉዳዮች የመሬት አጠቃቀም እና የሰብአዊ መረጃዎች ላይ የተሰጠ ትንታኔ
- ጥቅል የመረጃዎች ትንታኔ ሪፖርት

**መ) ሥራው የሚመለከተው**

- የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን
- አመራሩ
- ህዝቡ

**ሠ) ቁልፍ የማረጋገጫ ጥያቄዎች**

- ትንታኔ የሚሰጡባቸው ነጥቦች ተለይተው ትንታኔ ተሰጥቶአቸዋል?
- ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል?

**ረ) ለሥራው የሚያስፈልገው ቀን - 10 ቀን**

**ሰ) ዝርዝር ተግባራት**

## ተግባር 1. ትንታኔ የሚሰጥበትን ዘዴ መለየት

መረጃዎች ትንታኔ የሚሰጥባቸውን የስታትስቲክስ መሳሪያዎችን መለየት

- ለተፈጥሮአዊ ጉዳዮች
- ሰብአዊ ጉዳዮች
- ለማህበራዊ ጉዳዮች
- ለመሬት አጠቃቀም ስርጭት እና ድርሻ

## ተግባር 2. ትንታኔ የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች መለየት

መረጃዎችን ለመተንተን የምንጠቀምባቸው ፎርሙላዎች በእዝል አራት ላይ ተመልክቷል

➢ ፊዚካል እና አካባቢያዊ የሆኑ ጉዳዮች

### 1. የፊዚካል ጉዳዮችን መተንተን

- የገጠር ማዕከሏ የምትገኝበት ጂኦግራፊያዊ አቅጣጫ
- የመሬት ስፋት መጠን
- ተፈጥሮዓዊ ገፅታዎች
- ተዳፋትነት
- ቅርፅ
- የአየር ፀባይ

### 2. ሰብዓዊ እና ታሪካዊ ጉዳዮች

- ሥነ ህዝብ
- ታሪካዊ እና ባህላዊ(የባህል፣ የእምነትጉዳዮች…)

### 3. በገጠር ማዕከሏ ስላለው የማህበራዊ እና የመሰረተ ልማቶች አቅርቦት

- ትምህርት፣ ጤና.. ወዘተ
- መንገድ

- ➔ የመገናኛ መስመሮች
- ➔ መብራት
- ➔ ውሃ…

4. **በአካባቢው ስላለው የገጠር እና የከተማ ትስስር**

- ➔ የማህበራዊ እና የመሰረተ ልማት አገልግሎት ትስስር
- ➔ አስተዳደራዊ ትስስር
- ➔ የንግድ ትስስር

➢ **በመሬት ላይ ስላለው የመሬት አጠቃቀም ድርሻ መተንተን**

- ➔ ከመሠረታዊ ካርታ ላይ ጂአይ ኤስን በመጠቀም ነባራዊውን የመሬት አጠቃቀም ድርሻ መተንተን፡፡
- ➔ ትንታኔው የሰንጠረዥ ሪፖርትን ያካትታል

1. **የመኖሪያ ቤት**
   - የመኖሪያ መሬት ከጠቅላላው የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - የቤቶች አሰፋፈር እና ጥግግት
   - የመኖሪያ እና የሌሎች የመሬት አጠቃቀም መጣጣም
2. **ለገበያ እና የንግድ ተቋማት**
   - የንግድ የመሬት አጠቃቀም ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም
3. **የአስተዳደር አገልግሎት**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም
4. **የማህበራዊ አገልግለሎት መስጫ ተቋማት-**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም

5. **መዝናኛ፣ አረንጓዴ፣ እና ክፍት ቦታዎች**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም
6. **የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእርሻ ቦታ**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም
7. **የመንገድ እና ሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም
8. **የአነስተኛ ኢንዱስትሪ**
   - ከአጠቃላዩ የመሬት ስፋት አንፃር ያለው መጠን በመቶኛ
   - ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም አንፃር ያለው መጣጣም

## ተግባር 3. ስለተጠናቀሩት መረጃዎች ትንታኔ እና መግለጫ መስጠት

ለቀረቡ መረጃዎች ትንታኔ ለመስጠት በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች መምራት ይቻላል

➔መረጃዎችን በማጠናቀር ሂደት የተገኙ ጥሬ ሃቆችን ማስቀመጥ

➔ጥሬ ሀቆችን ከእውነታዎች ጋር ማነፃፀር

➔በንፅፅሩ መሰረት ወይም ያለውን እውነታ ማብራራት

➔እውነታዎች ስላላቸው እንደምታ ከፕላን ፅንሰ ሃሳብ አንፃር ገለፃ ማድረግ

➔በመጨረሻም በሚዘጋጀው ፕላን ውስጥ መሻሻል የሚገባቸውን በመጠቆም የመፍትሄ ሃሳብ መስጠት

## 2.5.4. ምዕራፍ/ Phase/ 4. የስኬች ፕላኑ ፅንሰ-ሃሳብ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

### ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት የገጠር ማዕከሏን መሠረታዊ ካርታ ላይ መሠረት በማድረግ የወደፊቱን የመሬት አጠቃቀም ድልድሎችን ለማሳዬት የሚያግዝ በሶስት ደረጃዎች የሚያልፍ በነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ መነሻ የሆነ አንኳር የመሬት አጠቃቀም ስዕላዊ የንድፍ ፅንስ ማዘጋጀት ነው፡፡ እነዚህም ሶስት ደረጃዎች አሁን አካባቢው ያለውን መነሻ መሠረታዊ ካርታ መያዝ፣ የተለያዩ አማራጭ የወደፊት የመሬት አጠቃቀም ድልድል ስዕላዊ መግለጫ ንድፍ እና የመንገድ ዲዛይኖች ማዘጋጀት ናቸው፡፡

### ለ) የዚህ ምዕራፍ ዋናዋና ተግባራት

**ተግባር 1.** የፕላኑን ፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

**ተግባር 2.** በተዘጋጀው የፕላኑን ፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ ላይ ውይይት ማድረግ

### ሐ) የሚጠበቁ ውጤቶች

- ➔ ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም መነሻ ድልድሎች የሚያሳይ የፕላኑን ፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ

### መ) ሃላፊነት የተሰጠው አካል

- የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን

### ሠ) ቁልፍ የማረጋገጫ ጥያቄዎች

### ረ) ለሥራው የሚያስፈልገው ቀን- 5 ቀን

### ሰ) ዝርዝር ተግባራት

**ተግባር 1. የፕላኑን ፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ ማዘጋጀት**

የገጠር ማዕከሉ የፕላኑን ፅንሰ ሃሳብ ማዕቀፍ ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡

- የገጠር ማዕከሉን መሠረታዊ ካርታ መያዝ
- የገጠር ማዕከሉ በቦታ ላይ ያለውን አቅጣጫ መለየት
- ዋናዋና የፕላን ድልድሎች አሁን ያሉበትን ቦታ መጠቆም
- የወደፊት የዕድገት አቅጣጫ መጠቆም
- አሁን ያለውን ዋና ዋና መንገዶችን መጠቆም
- ማዕከል ነው/ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ቦታዎችን መጠቆም
- ለገጠር ማዕከሏ ልማት ወሳኝ እና አስፈላጊ የሆኑ ቦታዎችን መለየት
- በገጠር ማዕከሏ ጥብቅ ቦታዎችን መለየት
- የመሬት አጠቃቀም ድልድልን ለይቶ በካርታ መንደፍ

**ተግባር.2. በተዘጋጀው ፅንሰ ፕላን ላይ ውይይት ማድረግ**

**1. ውይይቱን ማካሄድ**

- በፕላን ቡድኑ ውይይት ማካሄድ
- በፕላን ኮሚቴው እና በአመራሩ ደረጃ ውይይት ማካሄድ
- በምክክር መድረክ ደረጃ ውይይት ማካሄድ
- በውይይት የተነሱ ሀሳቦችን መረጃ መያዝ

**2. በውይይት የተነሱ ሃሳቦችን ማካተት**

- በውይይት የተነሱ ሃሳቦችን ማገናዘብ
- ዋጋ የተሰጠባቸውን የውይይት አስተያየቶችን መለየት
- በተሰጠው አስተያየት መሰረት የመሬት አጠቃቀም ድልድሉን ንድፍ መከለስ

## 2.5.5. ምዕራፍ/ Phase/ 5. ዋናውን የስኬች ፕላን ማዕቀፍ ማዘጋጀት

### ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት ከሀገሪቱ የእድገት አቅጣጫ አንፃር እና የገጠር ማዕከሉ ልማት ራዕይና ግብ ሊያሳካ የሚችል የወደፊት የመሬት አጠቃቀም ድልድሎችን እና የመሬት መጠን ማቀድ እና የገጠር ማዕከሏን ስኬች ፕላን ማዘጋጀት ነው፡፡

### ለ) የዚህ ምዕራፍ ዋናዋና ተግባራት

**ተግባር** 1. አስፈላጊ የሆኑ የመሬት ድልድሎችን መወሰን

**ተግባር** 2. የመንገድ መረቦችን መቅረፅ

**ተግባር** 3. በተዘጋጀው ዕቅድ ላይ የህሳብ ልውውጥ ማድረግ

**ተግባር** 4. የወደፊቱን የከተማ ፕላን በመስፈርት ልኬት መሠረት መቅረፅ

**ተግባር** 5. የገጠር የልማት ማዕከሏን የስኬች ፕላን ዝግጅት የተመለከተ አጠቃላይ የፁሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት

### ሐ) በዚህ ደረጃ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ➔ የመሬት አጠቃቀም ድልድል ስኬች ፕላን ዝግጅት
- ➔ የመሬት አጠቃቀም ድልድል ሪፖርት

### መ) ሃላፊነት የተሰጠው አካል

- ➢ የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን

### ሠ) ለሥራው የሚያስፈልገው ቀን - 8 ቀን

### ረ) መነሳት የሚገባቸው ቁልፍ ጥያቄዎች

- ለእያንዳንዳቸው አሰፈላጊ የመሬት ድልድሎች የተሰጠው የመሬት መጠን ተመጣጣኝ ነው?
- የመሬት አጠቃቀም ፕላን መሬት ላይ ካሉ መቆጣጠሪያ ነጥቦች ጋር ሲነፃፀር ያለው ዝንፈት ተፈትሿል?

## ሰ)ዝርዝር ተግባራት

### ተግባር 1. አስፈላጊ የሆኑ የመሬት ድልድሎች መወሰን

የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች የሳይት መምረጫ መስፈርት በአዝል አራት ተመልክቷል፡፡

➢ **በተሰበሰቡ መረጃዎች መሠረት ተመጣጣኝ የመሬት ድልድል ማድረግ**

በከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ ውስጥ የተቀመጠውን የ30፣30፣40 መርህን ግምት ውስጥ በማስገባት ለገጠር ማዕከላት በመነሻነት ሊያገለግል የሚችል የመሬት ድልድል በሰንጠረዥ ሁለት ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 2. ለገጠር የልማት ማዕከላት ፕላን ዝግጅት የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች ድርሻ**

| No. | ድልድሎች | መነሻ ድልድል በመቶኛ |
|---|---|---|
| 1 | የመኖሪያ | 20-25 |
| 2 | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | 10-20 |
| 3 | ገበያ እና ንግድ ማዕከላት | 3-7 |
| 4 | የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት | 10-20 |
| 5 | መዝናኛ፣ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች | 15-25 |
| 6 | ለአስተዳደር አገልግሎት | 2-5 |
| 7 | የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች | 15-30 |
| 8 | የአነስተኛ ኢንዱስትሪ | 5-10 |

**ምንጭ**: የጥናት ቡድኑ መነሻ ግምት

➢ **የገጠር ማዕከሏን የፕላን ወሰን መወሰን**

የገጠር የልማት ማዕከላት የፕላን ወሰን ስፋት ከ10 ሄክታር የማያንስ መሆን ያለበት ሲሆን ይህ የመሬት መጠን መወሰን ያለበት አስፈላጊ የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች በስተንዳርድ መሰረት በሚፈልጉት ልክ ከላይ በተቀመጠላቸው ድርሻ መሠረት በቀመር (Land budget) በተገኘው የጠቅላላው ድምር ውጤት መሆን አለበት፡፡

➢ **የመሬት ድልድሎችን ቦታዎች መጠቆም**

- የመኖሪያ
- የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት
- ገበያ እና ንግድ ማዕከላት
- የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት
- መዝናኛ፣ አረንጓዴእና እና ክፍት ቦታዎች
- ለአስተዳደር አገልግሎት
- የመንገድ እና የሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎቶች
- የአነስተኛ ኢንዱስትሪ

**ተግባር 2. የመንገድ መረቦችን መቅረፅ**

1. የመንገድ መረቦችን አቅጣጫ እና ጥግግት መወሰን
2. የመንገዶችን መጠን መወሰን እና መቅረፅ

- ዋና መንገድ( Principal arterial road) 20 - 25 ሜ (ነገር ግን የገጠር ማዕከሏን አቋርጦ የሚያልፍ አገር አቋራጭ ትልቅ መንግድ ካለ እና ይኸው መንገድ የገጠር ማዕከሉ ዋና መንድ ከሆነ ዋናው መንገድ በዚህ መንገድ ስፋት ልክ ሊሆን ይችላል)
- ዋና መንገድ መጋቢ(Sub - arterial raod) 15 - 20 ሜ
- ሁለተኛ መጋቢ መንገድ (Collector) 10-15 ሜ
- የውስጥ ለውስጥ መንገድ (Local) 8 - 12 ሜ

- (የመንገዶች ስፋት የእግረኛን እና የመንገድ ዳር ዛፍ መትከያ ቦታዎችን ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል)፡፡

3. የብሎክ መጠን መወሰን እና መቅረፅ

- ርዝመት 80ሜ - 150ሜ
- ስፋት 40 ሜ - 50 ሜ

4. የውሃ ተፋሰሶችን አቅጣጫ ለይቶ የመንገድ መረቦችን መቅረፅ

**ተግባር 3. በተዘጋጀው ንድፍ ፕላን ላይ የሀሳብ ልውውጥ ማድረግ**

- በፕላን ቡድኑ ውይይት ማካሄድ
- የውይይቶችን ሃሳብ መረጃ መያዝ

**ተግባር 4. የገጠር የልማት ማዕከሏን የወደፊቱን ስኬች ፕላን በመስፈርት ልኬት መሠረት መቅረፅ**

- ፕላኑን በ1፡5000 -1:2000 (በስትራቴጂ ሰነድ ላይ እንደተመለከተው) መስፈርት ልኬት መሠረት መቅረፅ
- የሀሳብ ልውውጥ ማድረግ
- የቀለማት ስታንዳርድ በመጠቀም የመጨረሻውን ቅርፅ መስጠት

ለዚህም የሚከተሉት የቀለማት ስታንዳርድ ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ አምስት ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 3 . የዋናዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች የፊደላትና የቀለማት ምልክቶች

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት (Letter) | ቀለማት (Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | | | | |
| 1 | መኖሪያ | ነባር የመኖሪያ ቤት | R-1 | ቢጫ | Horizontal hatch |
| | | የወደፊቱ የመኖሪያ ቤት ቦታ | R-2 | | |
| | | ከፍተኛ ጥግግት ያለበት ቦታ | R-3 | | |
| | | ልዩ ቤቶች (Special housing) | R-4 | | |
| | | | | | |
| 2 | ለገበያ እና ንግድ ተቋማት | ሱቆች | CBA-1 | ቀይ | Normal Square Hatch |
| | | ምግብ ቤቶች፣መጠጥ ቤቶች | CBA-2 | | |
| | | አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት | CBA-3 | | |
| | | የንግድ ማዕከላት | CBA-4 | | |
| | | ገበያ | CBA-5 | | |
| | | | | | |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት (Letter) | ቀለማት (Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| 3 | የማህበራዊ አገልግሎት | ትምህርት | S-1 | ሰማያዊ | 45° Hatch |
| | | መዋዕለ ህፃናት | S-11 | | |
| | | አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | S-12 | | |
| | | ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | S-13 | | |
| | | ጤና | S-2 | | |
| | | ጤና ኬላ | S-21 | | |
| | | ጤና ጣቢያ | S-22 | | |
| | | የህዝብ መገልገያ (Community & cultural facilities) | S-3 | | |
| | | የህፃናት እና የወጣቶች ማዕከል | S-34 | | |
| | | ማረፊያ ቦታ | S-42 | | |
| | | የህዝብ መፀዳጃ | S-43 | | |
| | | የማህበራዊ ደህንነት (እድር...) | S-44 | | |
| | | ለተለየ አገልግሎት የሚውሉ (Special functions) | S-5 | | |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት (Letter) | ቀለማት (Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | የታሪክ እና ቅርሳቅርስ ማዕከላት | S-52 | | |
| | | | | | |
| 4 | የመዝናኛ፣ አረንጓዴ እና ክፍት ቦታዎች | ክፍት ቦታዎች | EA-1 | አረንጓዴ | Square dotted |
| | | ስፖርት ሜዳዎች | EA - 83 | | |
| | | የአረንጓዴ መዝናኛ ቦታዎች | EA - 65 | | |
| | | አምልኮና የቀብር ቦታዎች | EA - 68 | | |
| | | የህፃናት መጫወቻ ቦታ | EA - 63 | | |
| 5. | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእረሻ ልማት | EA - 2 | አረንጓዴ | Square dotted |
| 6 | አስተዳደራዊ ተቋማት | መንግስታዊ ተቋማት | AD-1 | ቡናአይነት | |
| | | መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት | AD-2 | | |

| ተ.ቁ | የመሬት አጠቃቀም ድልድል | ዋና ዋና የመሬት አጠቃቀም ድልድል ይዘቶች | መለያ ፊደላት እና ቀለማት (Coding) | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ፊደላት (Letter) | ቀለማት (Color) | ጥቁር እና ነጭ |
| | | ንኡስ ፖሊስ ጣቢያ | AD-3 | | |
| | | የማህበራዊ ፍርድቤት | AD-6 | | |
| 7. | ኢንዱስትሪ | ኢንዱስትሪ | P-1 | ወይንጠጅ | አግድም የተሰመረበት ሳጥን |
| | | አነስተኛ ኢንዱስትሪ | P-3 | | |
| 8. | መንገድ | Road | RTU-1 | ግራጫ | |
| | | ዋና መንገድ | RTU-(PA) | | |
| | | የዋና መንገድ መጋቢ | RTU-(SA) | | |
| | | መጋቢ | RTU-(C) | | |
| | | የዉስጥ ለዉስጥ መንገድ | RTU-(L) | | |
| 9. | የመሠረተ ልማት እና ሌሎች አገልግሎቶች | የህዝብ ማመላለሻ መናኸሪያ | RTU-24 | | |
| | | የቧንቧ መሥመር | RTU-3 | | |
| | | የኤሌክትሪክ መሥመር | RTU-4 | | |
| | | የሥልክ መሥመር | RTU-5 | | |

ምንጭ፡ MUDC, 2012

## ተግባር 5. የገጠር የልማት ማዕከሏን የስኬች ፕላን ዝግጅት የተመለከተ አጠቃላይ የፁሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት

### 2.5.6. ምዕራፍ/ Phase/ 6. ፕላኑን ማስፀደቅ

**ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት**

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት የተዘጋጀው የገጠር ማዕከሉ ስኬች ፕላን ከፕላን መርህ አንፃር በመገምገም ለማፅደቅ ነው፡፡

**ለ) የዚህ ምዕራፍ ዋናዋና ተግባራት**

**ተግባር 1. ፕላኑን መገምገም**

**ተግባር 2. ፕላኑን ማፅደቅ**

**ሐ) ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች**

➔የገጠር የልማት ማዕከል አዲስ የፀደቀ ስኬች ፕላን

➔የገጠር ማዕከሏ የፀደቀ ፕላን የፁሐፍ ሪፖርት

**መ) ፈፃሚዎች እና ባለድርሻ አካላት**

የገጠር የልማት ማዕከል ስኬች ፕላን ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ እና ለማፅደቅ ባለድርሻ አካላት የሚከተሉት ናቸው

- የክልል የከተማ ልማት ቢሮ የፕላን የሥራ ሂደት/ ፕላን ኢንስቲትዩት፣ የዞን የፕላን የስራ ሂደት፣ የወረዳው ምክር ቤት እና የልማት ማዕከሉ አስተዳደር
- የፕላን ዝግጅት ኮሚቴ፣
- የልማት ማዕከሉ ህዝብ
- የፕላን ዝግጅት የቴክኒክ ቡድን

**ሠ) ለሥራው የሚያስፈልገው ቀን - ሦስት ቀን**

**ረ) ዝርዝር ተግባራት**

**ተግባር 1. ፕላኑን መገምገም**

- በተዘጋጀው ፕላን ላይ ለመወያት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን ማከናወን
- የተዘጋጀውን ፕላን ለውይይት ማቅረብ
- በውይይት ወቅት የተሰጡ አስተያዬቶችን ማካተት
- ፕላኑን የመጨረሻ ቅርፅ ማስያዝ

**ተግባር.2 ፕላኑን ማፅደቅ**

- በክልል የፕላን ተቋም ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ
- ፕላኑ እንዲጸድቅ የቅድመ ዝግጅት ሥራ መሥራት
- ፕላኑን ማፅደቅ

የገጠር ማዕከሉ የመጨረሻው ፕላን በክልሉ የከተማ ልማት ቢሮ፣ በዞን ምክር ቤት፣ በወረዳው አስተዳደር ፣ በቀበሌ ማዕከሉ አመራሮች እና በህዝቡ ውይይት ከተደረገበት በኋላ በወረዳው ምክር ይፀድቃል፡፡

- የጸደቀውን ፕላን ለሚመለከተው የወረዳ፣ የዞን እና የክልል መንግስት ማስረከብ
- የፕላን ኮፒ አባዝቶ ማሰራጨት
- በፕላን ኮሚቴው እና በቴክኒክ ቡድኑ የገጠር ማዕከሏ የፕላን ኮፒ በሚፈለገው መጠን እንዲባዛ በማድረግ ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ማሰራጨት ያስፈልጋል፡፡

## 2.5.7. ምዕራፍ / Phase/ 7. ፕላኑን መተግበር፣ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ

**ሀ) የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት**

የዚህ ምዕራፍ አስፈላጊነት በወረቀት ላይ በፁሑፍ እና በምስል (በካርታ) የተቀመጡ የገጠር ማዕከሉ የፕላን ጉዳዮችን ወደ መሬት ለማውረድ አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለመዘርዘር ሆኖ በዚህ ደረጃ የገጠር ማዕከሉ ፕላን በሂደት ወደ ተግባር የሚለወጥበት ደረጃ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍ ሌላው አስፈላጊ ተግባር የክትትል እና ግምገማ ሥራ ማካሄድ ነው፡፡ ይህም ሥራ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚከናወን ሆኖ የፕላን መርህዎችን፣ የመሬት አጠቃቀም ድልድሎች፣ ስታንዳርዶች እና ሌሎች በፕላን ማዕቀፉ የተቀመጡ ጉዳዮች በፕላኑ መሠረት መፈጸማቸውን ክትትል እና ግምገማ በማካሄድ ማረጋገጥ ነው፡፡

## ለ) ዋናዋና ተግባራት

ተግባር 1. የፕላን ትግበራ

ተግባር 2. የፕላን ትግበራ አባሪ ሪፖርት ማዘጋጀት

ተግባር 3. ክትትል ማድረግ

ተግባር 4. ግምገማ ማድረግ

## ሐ) በዚህ ደረጃ የሚጠበቁ ውጤቶች

- በወረዳ ደረጃ ፕላኑን ለማስተግበር የተዘጋጀ መዋቅር (በወረዳው መሬት አስተዳደር)
- የተቀጠሩ የቀያሽ ባለሞያዎች
- የፕላን ትግበራ የሚመራ ከወረዳው እና ከቀበሌ ማዕከሉ ምክር ቤት የተውጣጣ ቡድን ማቋቋም
- ለተግባሪዎች በፕላን ዝግጅት እና በሚመለከተው የስራ ሂደት ሥልጠና መስጠት
- ለክትትል የሚያግዝ የመከታተያ ቅፅ ማዘጋጀት
- በየጊዜው የሚደረጉ ሪፖርቶች
- በፕላን የምትመራ የገጠር የልማት ማዕከል

## መ) የዚህ ምዕራፍ ባለድርሻ አካላት

የዚህ ምዕራፍ ዋናዋና ባለድርሻ አካላት ፕላኑን ወደ መሬት ለማውረድ ሃላፊነት የሚኖረው የወረዳው የመሬት አስተዳደር ሲሆን የፕላኑን ትግበራ ክትትልና ግምገማ ለማከናወን የዞኑ ወይም የክልሉ የፕላን የሥራ ሂደቶች ናቸው፡፡

## ሠ) ለሥራው የሚያስፈልገው ቀን - 20 ቀን

## ረ) ዝርዝር ተግባራት

## ተግባር 1. የፕላን ትግበራ

### 1. የዝግጅት ሥራ

- ➔ በወረዳ ደረጃ በመሬት አስተዳደር የፕላኑን ትግበራ የሚመራ የሥራ ክፍል እንዲኖር ማድረግ
- ➔ በወረዳ ደረጃ በመሬት አስተዳደርና በአካባቢ ጥበቃ የፕላኑን ትግበራ የሚመራ ባለሞያ መመደብ
- ➔ ከወረዳው ምክር ቤት፣ ከቀበሌ ጽ/ቤት እና ከህዝቡ ተወካይ የተውጣጣ የፕላኑን ትግበራ በበላይነት የሚከታተል ኮሚቴ ማቋቋም
- ➔ በትግበራ ምዕራፍ ለተቋቋመው ኮሚቴ ስልጠና መስጠት
- ➔ በመሬት ላይ ድልድሉን ማሳየት
- ➔ ለህዝቡ ስልጠና መስጠት
- ➔ የአተገባበር መመሪያና ፕሮግራም ማውጣት

### 2. የትግበራውን ሂደት መምራት

- ➔ የትግበራውን ሂደት በተቀመጠው ፕላን መሠረት ለመምራት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- ➔ ለትግበራው ከተቀጠሩ የቴክኒክ ቡድን ጋር ምክክር ማድረግ
- ➔ ለትግበራው ዝክረ ተግባር በማዘጋጀት በጀት ማስፈቀድ
- ➔ ለትግበራው አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን እና ስታንዳርዶች ማጣቀስ
- ➔ ለትግበራው በወረዳ ደረጃ ዕቅድ ማውጣት
- ➔ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ማዘጋጀት
- ➔ አሰፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን መግዛት
- ➔ ባለሞያዎችን ማሰማራት

## 3. የትግበራውን ሥራ በቅየሳ መጀመር

1. በፕላኑ ላይ የተቀመጠውን የመሬት አጠቃቀም ድልድሎችን መለየት
2. ባለሞያዎች ለቀበሌ አስተዳደሮች የሚሰሩትን የስራ አይነትና አላማ በግልፅ ያስረዳሉ፣
3. የቀበሌ አመራሩ ከባለሞያዎች ጋርና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ውይይት ያካሂዳሉ፣
4. ባለሞያዎች የመሬት ላይ የቅኝት ሥራ ያከናውናሉ፡፡

- የገጠር ማዕከሉን ዙሮ መመልከትና ግንዛቤ መያዝ
- መቆጣጠሪያ ነጥቦች/bench marks/ የሚተከሉባቸውን ቦታዎች መለየት/መወሰን
- ሌሎች ቀጥታ ወደሽንሻኖ ስራ ለመግባት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን መያዝ

5. የቅየሳ መሳሪያዎችን በመጠቀም የቅየሳ ሥራ በማከናወን የማዕዘን ድንጋዮችን መትከል

6. በተቀመጠው የመሬት አጠቃቀም መሠረት የብሎክ እና ሌሎችን የመሬት ሽንሻኖዎችን ማከናወን

- ርዝመት 80ሜ - 150ሜ
- ስፋት 40 ሜ - 50 ሜ

7. መንገድ የመክፈት ሥራ ማከናወን

- ዋና መንገድ( Principal arterial road) 20 - 25 ሜ
- ዋና መንገድ መጋቢ(Sub - arterial raod) 15 - 20 ሜ
- ሁለተኛ መጋቢ መንገድ (Collector) 10-15 ሜ
- የውስጥ ለውስጥ መንገድ (Local) 8 - 12 ሜ

8. ለተለያዩ ዓላማዎች የሚውሉ ብሎኮች በመለየት በፕላኑ ላይ በተቀመጠው የመሬት አጠቃቀም ድልድሎችን መሠረት ምደባ የመስጠት ስራ በማከናወን በሂደት ማልማት

- የመሬት ድልድሎችን በመሬት ላይ ማሳዬት
- የመሬት ድልድሎችን በመሬት ላይ በማሳዬት ሂደት በፕላኑ ምክንያት በግለሰቦች የግል ይዞታ ለሚደርሱ ጉዳቶች በመሬት ሽግሽግ እንዲካሱ ማድረግ
- ከወረዳውና ከዞኑ መስተዳድር ጋር መመካከር

## ተግባር 2. የፕላን ትግበራ አባሪ ሪፖርት ማዘጋጀት

የፕላን ትግበራው በመሬት ሽንሻኖ ከተከናወነ በኋላ የስራውን ሂደት የሚተነትን አጭር የፁሑፍ ሪፖርት መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የሪፖርቱ ይዘትም የሚከተለው ይሆናል፡፡

1. መግቢያ
2. የትግበራው ዓላማ
3. የትግበራው አስፈላጊነት
4. የፕላን ትግበራው የተከናወነበት ስልት
5. የፕላን ትግበራው ያካተታቸው የመሬት አጠቃቀሞች በዝርዝር
6. የሽንሻኖ ፕላኑ አፈፃፀም

- የተከናወኑ ምክክሮች
- ለስንት ዓመት እንደሚያገለግል
- የይዞታ ማረጋገጫ
- በባለቤትነት የሚያስፈፅም አካል
- የወደፊት የትኩረት አቅጣጫ እና አፈፃፀም

## ተግባር 3. ክትትል ማድረግ

### 1. ክትትል ማድረግ

- በትግበራ ምዕራፍ የክትትልና ግምገማ ሥራ የሚከናወነው በዞን የፕላን የሥራ ሂደት ሲሆን ከዞኑ አቅም በላይ ለሆኑ ጉዳዮች ወደ ክልል የፕላን ተቋም ተመርቶ በዚያው አግባብ ይፈፀማል፣ በልዩ ወረዳዎች ለሚከናወን የፕላን ትግበራ ክልሉ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፡፡
- የክትትል እና ግምገማ ኮሚቴ በወረዳው ምክር ቤት በማቋቋም በዞኑ ካለው መንግስታዊ መዋቅር ጋር የሥራ ግኑንኙነት በመፍጠር ማከናወን ይቻላል፡፡
- ለክትትልና ግምገማ ኮሚቴው ስልጠና መስጠት
- ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የገንዘብ እና የግብዓት አቅርቦት ማዘጋጀት
- ለክትትል ሥራ የሚሆኑ አስፈላጊ ቅፆችን ማዘጋጀት
- አስፈላጊ መረጃዎችን ማሰባሰብ
- መረጃዎችን መተንተን
- ወቅቱን የጠበቀ ተከታታይ ሪፖርት ቢያንስ በየሩብ ዓመት ለዞን የፕላን የሥራ ሂደት ማቅረብ

## ተግባር 4. ግምገማ ማድረግ

### 1. ግምገማ ማድረግ

በዚህ ክፍል ዋናው ተግባር የገጠር የልማት ማዕከሏ የፕላን ዝግጅትና ትግበራ በልማት ማዕከሉ ላይ ያመጣውን ፋይዳ መገምገም እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ነው

- ከላይ ለክትትል ሥራ የተቋቋመው ቡድን የግምገማ ሥራውንም ያከናውናል
- በፕላን አፈፃፀም ግምገማ ላይ ስልጠና መስጠት
- የግምገማ ማዕቀፎችን መቅረፅ

- የግምገማ ቅፆችን ማዘጋጀት
- የግምገማ መረጃዎችን ማሰባሰብ
- መረጃዎችን መተንተን
- ወቅቱን የጠበቀ ተከታታይ ሪፖርት ቢያንስ በየዓመቱ ለዞን የፕላን የሥራ ሂደት ማቅረብ

# ክፍል ሦስት. ተያያዥ ሕጎችና ማንዋሉን የማስተግበር አቅም

## 3.1.የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች

### 3.1.1 የከተማ ልማት ፖሊሲ

በ1998 ዓ.ም.በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ የወጣው የከተማ ልማት ፖሊሲ እንዳስቀመጠዉ የከተማ ፕላን አጠቃላይ አቅጣጫ የገጠርና ከተማ እንዲሁም የከተማ እና ከተማ ትስስርን መሰረት ያደረገና የሚያጠናክር፣ የልማት እቅድንና የመሬት አጠቃቀምን የሚያቀናጅ፣ የሃገርና የክልል የልማት እቅዶችን መነሻ የሚያደርግ ይሆናል ይልና ህዝቡም የልማት ባለቤት መሆኑም መረጋገጥ ይኖርበታል የሚለዉን ያስቀምጣል፡፡

የፕላን አፈፃፀሙም የተቋማዊ አቅም ግንባታና በጀትን አብሮ ያቀደ፣ በማስፈፀም ህግ የተደገፈ፣ ግልፅነትንና ተጠያቂነትን ያረጋገጠ መሆን አለበት፡፡ ይህም በቀጣይነት የሚሻሻልና በዝርዝር ማስፈፀምያ ፕላን እንዲደገፍ በማድረግ ህያዉና ሊተገበር የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም የሚዘጋጀዉ የከተማ ፕላን ከተሞችን በስርአት ለማሳደግና የልማት ማእከልና ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያግዝ እንዲሁም ለኑሮና ለስራ አመቺ ለማድረግ የሚረዳ መሆን አለበት የሚለዉ ይገኝበታል (ከ.ል.ኮ.ሚ ፣1998 ዓ.ም)፡፡

### 3.1.2 የከተማ ፕላን ህግ

በ2000 ዓ.ም የወጣዉ የከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000 እንዳስቀመጠዉ የከተማ ፕላን አዋጁ አስፈላጊነት የተመጣጠነና የተቀናጀ ብሄራዊ፣ ክልላዊና አካባቢያዊ ዕድገት ማምጣት ይቻል ዘንድ ፕላን ሳይኖራቸዉ ቁጥራቸዉ እየጨመረ የመጡ ከተሞችን ትክክለኛና ራዕይ ባለዉ የከተማ ፕላን መቆጣጠር አስፈላጊ መሆኑን ካብራራ በኋላ የመንግስትም ሆነ የግል ያገባኛል ባዮች አገር አቀፍ መስፈርቶችን በጠበቀ አኳኋን የከተማ ፕላን ሃሳብ ማመንጨትን፣ አዘገጃጀትንና አፈፃፀምን አስመልክቶ በሚደረገዉ የአሰራር ሂደት ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን በመግለፅ የአዋጁ የሚከተሉትን መርሆዎች አሰቀምጧል፡፡

በዚህ አዋጅ መሠረት ማናቸውም የከተማ ፕላን ዝግጅት የሚመነጭበትና ፕላን የሚዘጋጅበት ሂደት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡-

- **ሀ) የፕላኖችን ተዋረድ መጠበቅ**
- **ለ) በአንድ አገራዊ ራዕይና ስታንዳርድ እንዲሰራና ተፈጻሚነት ያለው ሆኖ መገኘት፣**
- ሐ) የከተሞች የርስበርስ ትስስርና የከተማና ገጠር ግንኙነት ግምት ውስጥ ማስገባት፣
- መ) ውጤታማ የመሬት አጠቃቀምን ታሳቢ አድርጎ የከተሞችን ወሰን መከለል፣
- ሠ) በከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ወቅት የህዝብ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲኖር ማድረግ፤
- ረ) የማሕበረሰብና ያካባቢ ደህንነትን መጠበቅ፣
- ሰ) ዘላቂ ልማትን የሚያረጋግጥ ሆኖ መገኘት፣
- ሸ) የታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች እና እንክብካቤ እና ጥገና ማግኘት
- ቀ) የህዝብ እና የግል ፍላጎት ተጣጥሞ መገኘት

### 3.1.3. የከተማ ፕላን ዝግጅትና አተገባበር ስትራቴጂ

በ2006 ዓ.ም. የፀደቀው የከተማ ልማት፣ ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ ከከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅትና አተገባበር ጋር በተያያዘ እየገጠሙ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ያስችል ዘንድ የተለያዩ የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት መፍትሄ ከመስጠት አንፃር የሚከተሉትን የፕላን አይነቶች በተለያዩ የከተማ ፈርጅ ውስጥ ላሉ ከተሞች እንዲዘጋጁ አመልክቷል፡፡ በስትራቴጂው የታቀፉ የፕላን መሳሪያዎች እና አይነቶች፡፡

ሀ) የመሰረታዊ ካርታ (Base Map)
ለ) የመዋቅራዊ ኘላን (Structural Plan)
ሐ) የስትራቴጂያዊ ፕላን (Strategic Plan)
መ) የመሠረታዊ ኘላን (Basic Plan)
ሠ) የስኬች ኘላን (Sketch Plan)

ከላይ ከተዘረዘሩ የፕላን ዓይነቶች አንዱ የስኬች ፕላን ሲሆን ይህም የፕላን አይነት የሚዘጋጀው በፈርጅ ስድስት ውስጥ ላሉ ገጠር የልማት ማዕከላት እንደሆነ ስትራቴጂው ያመለክታል፡፡

በዚህም የስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ የገጠር የልማት ማዕከላትን አስመልክቶ የሚከተሉትን ዋናዋና የፕላን ማዕቀፎችን አሰቀምጧል፡፡

- የገጠር የልማት ማዕከላት ዘርዝር ያለ የመሬት አጠቃቀም የሚያሳይ መሠረታዊ ኘላን እስከሚዘጋጅላቸው ድረስ ዕድገታቸውን በስርዓት ለመምራት የሚያስችል አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያመላክት ስኬማቲክ ኘላን እንዲኖራቸው ማድረግ እንደሚያስፈልግ
- የገጠር የልማት ማዕከላት በፈርጅ ስድስት ውስጥ እንደሚካተቱ እና እነዚህም ከተማ ቀመስ የልማት ማዕከላት የሚዘጋጅላቸው ስኬች ኘላን መሆኑ
- ስኬች ኘላን ከ5-10 ዓመት ለሚሆን የኘላን ዘመን በ1፡5,000 መስፈርት መዘጋጀት እንዳለበት ፡፡
- ስኬች ኘላን ዝርዝር የመሬት አጠቃቀም ኘላን ማዘጋጀት ሳያስፈልግ ዋና ዋና የሆኑ የመሬት አጠቃቀም ምድቦችን ብቻ የሚያሳይ መሆን እዳለበት፡፡

- በዚሁ መሠረት የሚዘጋጀው ኘላን የመኖሪያ አካባቢዎችን የሚያሳይና እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ለመኖሪያ የሚሰጠውን የቦታ ስፋት ተከትሎ በብሎክ ደረጃ የሚዘጋጅ፣ የገጠር ቀበሌ መስተዳድርና የፖሊስ ማዕከላት የሚያመላክት፣ ለሱቆችና የከብት ገበያ እንዲሁም ለሳምንት ገበያ የሚሆኑ ቦታዎችን የሚያሳይ፣ ለትምህርት ቤት፣ ለጤና ኬላና ለአምልኮ የሚሆኑ ቦታዎችን የሚያመላክት፣ በተለያዩ ምክንያቶች ለከተማ አገልግሎት ሊውሉ የማይችሉ ቦታዎችን የሚያስጠብቅ እና መንገዶችን የሚያሳይ መሆን እንዳለበት፡፡
- መንገዶችን በተመለከተ በተለይም በዋና፣ ዋና መንገዶች ላይ ላሉ ማዕከላት ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት እየተጠና ካለው የአገራዊ ስርዓተ ከተማ (National Urban System) ውጤት ጋር በተገናዘበ መልኩ ወደ የማዘጋጃቤት አገልግሎቶች የሚሰጥ ከተማነት የማደግ እድል ካላቸው፣ ነገሮችን አርቆ በማየት እንደማንኛቸውም ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ መንገድ ይሰራ ዘንድ በቂ የመንገድ ወሰንና ክልል ማስጠበቅ እንደሚገባ እና የመንገዶች ስፋትም ከ20 ሜትር እስከ 8 ሜትር በተዋረድ መቀመጥ እንደሚኖርበት የሥትራቴጂው ሰነድ ያመለክታል (ከልቤኮሚ፣ 2006 ዓ.ም)፡፡

### 3.1.4. የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ

የመንግስትን አገራዊ የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድን እና የሴክተሩን አዲስ አደረጃጀትና የአመራር ለውጥ ተከትሎ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የመንግስትን የልማት አቅጣጫ በአግባቡ ለመምራትና ተግባራዊ ለማድራግ በአምስት ዓመታት ከ2003-2007 ዓ.ም ተግባራዊ የሚሆን ክፍለ-ኢኮኖሚያዊ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማዘጋጀቱ ይታወቃል፡፡

የከተማ ፕላን ዕዳት እና ውበት ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም በሁለተኛ ደረጃ አነስተኛ ከተሞች በፕላን እንዲመሩ በማድረግ እድገታችውን ለማፋጠን እና የገጠር- ከተማ እና የከተማ- ከተማ ትስስርን ለማፋጠን የአነስተኛ ከተሞች ልማት ፕሮጀክት ተቀርጾ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት አንደኛው ግብ መሠረታዊ ካርታ ለሚዘጋጅላቸው አነስተኛ ከተሞች ወይም እያቆጠቆጡ ላሉ የገጠር ማዕከላት ክትትል እና ድጋፍ ማደረግ የዕቅድ ዘመኑ ተግባዊ እንደሆን ተቀምጦ ነበር፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመንም (2008-2012) 8 ሺህ ለሚደርሱ የገጠር ማዕከላት ፈርጃቸውን መሠረት ያደረገ ፕላን እንዲዘጋጅላቸው እና ተግበራዊ እንደሚደረግ ዕቅድ ይዟል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የዕቅድ ሰነዱ የከተማ ፕላን ዝግጅት እና አፈፃፀም አቅምን ለማሳደግ የተለያዩ ስልቶችን ያመለከተ ሲሆን ከተቀመጡ ስልቶች ከፊሉ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) የከተሞች/ የገጠር ማዕከላት ዕድገት በፕላን የተመራ እንዲሆን ህግን፣ መመሪያዎችን እና ማንዋሎችን ተከትሎ እንዲፈፀም የአስፈፃሚ አካላት የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን፤

ለ) የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 3.2. ማንዋሉን ለማስተግበር የሚያስፈልገው የማስፈጸም አቅም ዝርዝር

### 3.2.1. የሰው ሃይል

የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የፕላን ዝግጅት እና ትግበራን ለመምራት የሚያስፈልጉ የቡድን አባላት እና የሙያ ስብጥር የሚከተሉትን ያካተተ ቢሆን ይመረጣል፡፡

**ሀ) አንድ የስፓሻል ፕላነር** (የከተማ ፕላን ባለሞያ ወይም አርኪቴክት ወይም ስፓሻል ፕላነር ወይም የከተማ ዲዛይን ባለሞያ)፡፡

**ለ) አንድ የፊዚካል ፕላነር** (የጂኦግራፊ ወይም ጂኦሎጂ ወይም እንቫይሮመንት ባለሞያ)፡፡

**ሐ) አንድ የቅየሳ ባለሞያዎች** (የሰርቬይንግ ምህንድስና ባለሞያዎች)

**መ) ሁለት የቅየሳ ረዳት ባለሞያዎች** (የቴክኒክ እና ሙያ ደረጃ አንድ የቅየሳ ባለሞያ)

**ሠ) አምስት የጉልበት ሰራተኞች** (ከልማት ማዕከሉ ነዋሪዎች)

### 3.2.2. ለስራው አስፈላጊ የሆነውን ሃይል ማደራጀት እና መመደብ

ሀ) የፕላን ዝግጅትና ትግበራ ኮሚቴ

ለ) የፕላን ዝግጅት እና ትግበራ የቴክኒክ ቡድን ማደራጀት

- የፕላን ዝግጅት የቴክኒክ ቡድን
- የዞኑ የፕላን የስራ ሂደት
- የወረዳው የመሬት አስተዳደር
- የቀበሌው የገጠር መሬት አስ/አጠቃቀም ባለሙያ
- የቀበሌው ስራአስኪያጅ
- የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ

ሐ) የፕላን ዝግጅት ትግበራ የቴክኒክ ቡድን መሪ (የፕላን ወይም የቅየሳ ባለሞያ)

### 3.2.3. አደረጃጀት

**የገጠር ማዕከላት የፕላን ዝግጅት እና አፈጻጸም መዋቅር**



### 3.2.4. ማንዋሉን ለመተግበር ተፈላጊው የቴክኖሎጂ ድጋፍ

በፕላን ቅድመ ዝግጅት ወቅት አሰፈላጊ የሆኑ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪዎቸን ለመቀረጽ እና በፕላን ዝግጅት ወቅት ከሳተላይት ወይም በመሬት ላይ ቅየሳ ዘዴ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማጠናቀር እና ለመተንተን ተፈላጊው የቴክኖሎጂ አቅርቦት

ሀ) ኮምፒውተር ሃርድዌር እና ሶፍት ዌር (ዎርድና ኤክሴል) የፁሑፍ መረጃዎችን ለማጠናቀር ጥቅም ላይ ይዉላል፡፡ ይሁንና የገጠር ማዕከሉ ነባራዊውን እና የወደፊቱን የመሬት አጠቃቀም ድልድልን ለመተንተን ጂ አይ ኤስ ጥቅም ላይ ሲውል አውቶካድ ሶፍት ዌር ደግሞ ፕላኑን ለማዘጋጀት ያገለግላል፡፡

ለ) የቅየሳ መሳሪያዎች

1. ቶታል ስቴሽን ወይም ሌሎች የቅየሳ መሳሪያዎችን በጥምር በመጠቀም (ቴዶላይት፣ ጂፒኤስ፣ ሌቨሊንግ እና የመሳሰሉትን)
2. የህትመት መሳሪያዎች ለምሳሌ ፕሎተር፣ ስካነር እና የመሳሰሉትን
3. ሌሎች መሳሪያዎች-
    - የርዝመት መለኪያ ሜትር
    - ጃሎን
    - የእጅ ካልኩሌተር
    - የሂሳብ የጂኦሜትሪ መሳሪያዎች
    - የስቴሽኔሪ መሳሪያዎች
4. የሳተላይት ምስል ከተገኘ የመሠረታዊ ካርታ ዝግጅት ለማከናወን ፎቶግራሜትሪክ ዎርክ ስቴሽን /Supper computer for 3D/ ጥቅም ላይ ይውላል
5. ተሽከርካሪ

### 3.2.5. የስኬች ፕላን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር አስፈለጊው የጊዜ መጠን

የስኬች ፕላን ለማዘጋጀት እና ለመተግበር አስፈላጊው የጊዜ መጠን እስከ ዘጠና ቀን ነው፡፡

# ክፍል አራት.የማንዋሉ አፈጻጸም ደረጃ

## 4.1. ማንዋሉን ስለማሻሻል

ይህ የስኬች ፕላን ማዘጋጃ ማንዋል አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፣

## 4.2. ማንዋሉ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ማንዋሉ ለሚኒካቢኔ ቀርቦ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

---

**መኩሪያ ኃይሌ**

**የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር**

**ሚኒስትር**

# ማጣቀሻዎች


- ኢ.ፌ.ድ.ሪ (1987)፡ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት
- ኢ.ፌ.ድ.ሪ (2000)፡ የከተማ ፕላን አዋጅ ቁጥር 574/2000
- ከ.ል.ኮ.ሚ. (1998)፡ የኢትዮጵያ ከተማ ልማት ፖሊሲ
- ከ.ል.ኮ.ሚ. (2005) ፡ የከተማ መሬት አጠቃቀም ፕላን ዝግጅት እና አፃፀም ስትራቴጂ (ረቂቅ)
- ከልቤኮሚ (2006 ዓ.ም)፡ የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ
- የከ.ል.ኮ.ሚ (2003)፡ ክፍለ - ኢኮኖሚ የአምስት አመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ
- የአማራ ክልላዊ መንግስት (2003 ዓ.ም)፡ የአማራ ክልል የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የሽንሻኖ ፕላን ለሚያዘጋጁ ባለሞያዎች ስልጠና ለመስጠት የተዘጋጀ ማንዋል
- የአማራ ክልላዊ መንግስት (2005 ዓ.ም)፡ የአማራ ክልል የገጠር ቀበሌ ማዕከላት የመሬት አቅርቦት አስተዳደርና አጠቃቀም መመሪያ
- **Bartone, Carl, Janis Bernstein, Josef Leitmann and Jochen Eigen**: (1994): Toward Environmental Strategies for Cities: Policy Considerations for Urban Environmental Management in Developing Countr ies. Washington: World Bank. Report 18, Urban Management Programme.
- **Daffa J.M, Bayer T.G and Kamalia S.K (2003):** Land Use Planning Manual for Coastal Tourism Development in Tanzania, Training Module
- **Haines, Anna and et al(2005):** A guide to preparing the land use element of a local comprehensive plan
- **MUDC (2012)**: Revised Standard for Structure Plan Preparation and Implementation.
- MUDH (2016)፡ National Urban Development Spatial Plan, National Urban System study.
- **MUDC (2012):** Structur Plan Manual (Revised version) A.A.

- **Oromia Regional State (2012):** A manual For Preparation and Implimentation of Basic Plan for Rural Growth Center.
- **NUPI (2004): የከተማ ፕላን አዘገጃጀት አፈፃፀም ችግሮች እና የመብትሔ አቅጣጫዎች**
- **Smith, Herbert H. (1993):** The Citizen's Guide to Planning (3rd ed.) Chicago; American Planning Association. +267pp.
- **Taylor, J.L. and D.G. Williams. (1982):** "Problems and Issues in Asian Urban Areas and the Response of Planning Practice." Pp. 3-45. In Urban Planning Practice in Developing Countries. John L. Taylor and David G. Williams (eds.) Toronto: Pergamon Press. +357pp.
- **United Nations (1990) :** Human Development Report: Oxford University Press
- **United Nations (1991)** : World Urbanization Prospects, New York
- **United Nations (2011):** World urbanization prospects: The 2011 revision.
- **United Nations Population Division. 2002:** New York. http://www .un.org. Accessed on September 2012.
- **United Nations (2002).** Press Release, POP/815, 21 March, pp-
- United Nations (2015). World Population Prospects: The 2015 Revision.

# እዝሎች

## እዝል 1 ፦ ለገጠር የልማት ማዕከላት ስኬች ፕላን ለማዘጋጀት የሚረዱ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆች/ቸክ-ሊስቶች፡

1. ተፈጥሮአዊ መረጃዎች

1.1. የማዕከሏ የመሬት አቀማማጥ ስፋት እና ቅርጽ ምን ይመስላል ?

..............................................................................................................

1.2. በማዕከሏና በአካባቢው የሚገኙ ዋናዋና የመሬት ገፅታዎች፦ ተራራዎች፣ ኮረብታዎችና ሜዳማ ቦታዎች... በሰንጠረዥ ቢገለፁ?

| ተ.ቁ | የተራራማ/ኮረብ ታማ ስም | ከፍታ /ከባህር ጠለል በላይ በሜትር | የሚያዋስናቸው አካባቢዎች | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ተራራ/ጋራ/ | | | |
| 2 | ኮረብታ /ጉብታ/ | | | |
| 3 | ሜዳ | | | |
| 4 | | | | |

*ማሳሰቢያ፦ አስተያየት በሚለው ስር ደን የለበሰ ፣የተሸረሸረ፣ አለታማ፣ ወዘተ በማለት የአካባቢውን ገጽታ በማሳየት ይገለፅ ""*

1.3. በልማት ማዕከሏ የውሃ አካላት፣ በደን የተሸፈኑ እና የረግረጋማ ቦታዎች ድርሻ ምን ያህል ነው ?

..............................................................................................................

1.4. የገጠር የልማት ማዕከሏ የምትገኝበት ጂኦግራፊያዊ እና ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር ያላት አንጻራዊ አቅጣጫ የት ነው ?

..............................................................................................................

1.5. የማዕከሏ የወደፊት የመስፋፊያ አቅጣጫ ወዴት ነው ?

..............................................................................................................

1.6. የገጠር ማዕከሏ የአፈር አይነት ምን አይነት ነው ?

…………………………………………………………………………………………

1.7. ከማዕከሏ ተፈጥሮአዊ አቀማመጥ ጋር የተያያዙ ዋናዋና ችግሮች ምንድን ናቸው ?

(ጎርፍ፣ ናዳ ….) ……………………………………………………………………

1.8. የገጠር የልማት ማዕከሏ የአየር ንብረት ሁኔታ ምን ይመስላል

- የዓመቱ አማካኝ የሙቀት መጠን ……………………………………..
- የዓመቱ አማካኝ የዝናብ መጠን ……………………………………..

**2. ሰው ሰራሽ /ነባራዊ የመሬት አጠቃቀም/ መረጃዎችን ጂአይኤስን በመጠቀም ከሳተላይት ምስል ወይም ከመሬት ላይ የቅየሳ መረጃ ውጤት መረጃ መሰብሰብ**

1.1. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ የመኖሪያ መሬት ሽፋን ምን ያህል ድርሻ አለው ?

…………………………………………………………………………………

1.2. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ የመኖሪያ አካባቢ ግብርና እና የእርሻ ቦታ ሽፋን ምን ያህል ድርሻ አለው ?

…………………………………………………………………………………

1.3. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ ለአስተዳደር ተቋማት አገልግሎት መስጫ የዋለው ቦታ ምን ያህል ነው ?

…………………………………………………………………………………

1.4. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ ለገበያ እና የንግድ ተቋማት አገልግሎት መስጫ የዋለው ቦታ ምን ያህል ነው ?

…………………………………………………………………………………

1.5. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት የዋለው ቦታ ምን ያህል ነው ?

…………………………………………………………………………………

1.6. ከገጠር ማዕከሏ ጠቅላላ ቦታ ለመንገድ እና ለሌሎች መሠረተ ልማት አገልግሎት የዋለው ቦታ ምን ያህል ነው ?

.............................................................................................................

1.7. የመዝናኛ፣ አረንጓዴ፣ እና ክፍት ቦታዎች ጠቅላላ ሽፋን ምን ያህል ነው ?

.............................................................................................................

1.8. ለሌሎች አገልግሎቶች የዋለውስ ? ....................................................

**2. ሰብዓዊ መረጃዎች**

**2.1. የሥነ-ሕዝብ መረጃዎች**

2.1.1. የገጠር የልማት ማዕከሏ ጠቅላላ የነዋሪ ህዝብ ብዛት ስንት ነው ?

ወንድ ................. ሴት .................. ድምር ..................

2.1.2. የገጠር የልማት ማዕከሏ የህዝብ ቁጥር በዕድሜና በጾታ ስብጥር ቢገለፅ?

.........................................................................................................

**2.2. ታሪካዊና ባህላዊ መረጃዎች**

2.2.1. የገጠር ማዕከሏ መቸ፣ በማን እና እንዴት ተመሰረተች? ለመቆርቆር ምክነያት የሆኑትስ ምንድን ናቸው ?

.........................................................................................................

2.2.2. የገጠር ማዕከሏ ስትመሰረት ሌላ ስም ነበራት? ማን ትባል ነበር ? ትርጓሜውስ?

.........................................................................................................

2.2.3. የአሁኑን ስያሜዋንስ መቸ አገኘች ? ትርጓሜውስ ?

.........................................................................................................

2.2.4. በአካባቢው ከፍተኛ በዓላት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?

.........................................................................................................

2.2.5. በአካባቢው የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች አሉ ? ካሉ ለምን ታሪካዊ ተባሉ ?

……………………………………………………………………………………………

2.2.6. በአካባቢ የሚገኙ ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ ቅርሶች አሉ? ካሉ ምን ምን ናቸው ? ……………………………………………………………………………

## 3. ከገጠር ማዕከሏ ትስስር ስላላቸው አካባቢዎች መረጃ መሰብሰብ

3.1. የገጠር ማዕከሏ ከአጎራባች ከተሞችና ገጠር ማዕከላት ጋር ያላት መልካምድራዊ ቀረቤታ ቢገለጽ?

……………………………………………………………………………………………

3.2. ማዕከሏ በአቅራቢያዋ ካሉ ከተሞችና የገጠር ማዕከላት ጋር ያላት የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር ምን ይመስላል?

……………………………………………………………………………………………

3.3. ማዕከሏ በአቅራቢያዋ ከሚገኙ ከተሞችና ገጠሮች ጋር ያላት የግብርና ምርት ውጤቶች አቅርቦትና የገበያ ትስስር ምን ይመስላል?

……………………………………………………………………………………………

3.4. ማዕከሏ ከአቅራቢያዋ ካሉ ከተሞች እና የገጠር ማዕከላት ጋር ያለው የመሰረተ ልማት ትስስር ምን ይመስላል ?

……………………………………………………………………………………………

3.5. በማዕከሏ አቅራቢያ በመካሄድ ላይ ያሉ የልማት ፕሮጀክቶች አሉ ?

……………………………………………………………………………………………

3.6. በማዕከሏ በአቅራቢያዋ ካሉ የገጠር ቀበሌዎች ጋር የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ አገልግሎቶች አሉ?

……………………………………………………………………………………………

3.7. በማዕከሏ በዙሪያዋ ላሉ አካባቢዎች አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ እና የቱሪዝም አገልግሎቶች ይገኛሉ ?

……………………………………………………………………………………………

# 4. የማህበራዊ አገልግሎት መረጃዎች

## 4.1. ትምህርት

4.1.1. በማዕከሏ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች በአይነት፣ በስም እና ብዛታቸው ስንት እንደሆነ ቢጠቀስ ? የተመሰረቱበት ጊዜስ መቸ ነው ?

..........................................................................................

4.1.2. በማዕከሏ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከባለቤትነት አንጻር ተለይተው ቢቀመጡ ? የመንግስት ................ የግል ................. ሌሎች ካሉ ........................

4.1.3. የትምህርት ቤቶቹ ስፋት በካ.ሜትር ምን ያህል ነው ?

..........................................................................................

4.1.4. ትምህርት ቤቶች የመስፋፊያ ቦታ አላቸው ?

..........................................................................................

## 4.2. ጤና

4.2.1. በማዕከሏ የሚገኙ የጤና ተቋማት አይነትና ብዛት ቢገለፁ ?

..........................................................................................

4.2.2. የጤና ተቋሙ የሸፈነው ቦታ በካ.ሜትር ምን ያህል ነው ?

..........................................................................................

4.2.3. የጤና ተቋማቱ የመስፋፊያ ቦታ አላቸው ?

..........................................................................................

## 4.3. የአምልኮ ቦታዎች

4.3.1. በማዕከሏ ስንት ቤተክርስትያኖችና መስጊዶች አሉ? የሚሸፍኑት የቦታ ስፋት ምን ያህል ነው? ህብረተሰቡ በይዞታዎች ላይ ይስማማል ? ካልተስማሙ ለምን? ..........................................................................

4.3.2. የአምልኮ ስፍራዎች ይዞታ በቂ ነው ?

……………………………………………………………………………………

## 4.4. የመቃብር ቦታዎች

4.4.1. በማዕከሏ ያለው የቀብር ቦታ የይዞታ ስፋት ምን ያህል ነው ? የቀብር ቦታው ተስማሚ ነው ? ከህብረተሰቡ ፍላጎት አንፃር ቢገለፅ ?

……………………………………………………………………………

4.4.2. በማዕከሏ ተጨማሪ የቀብር ቦታ ፍላጎት አለ ?

……………………………………………………………………………

4.4.3. የቀብር ስፍራ የሌለው ሀይማኖት አለ ?

……………………………………………………………………………

## 4.5. የመዝናኛ ቦታዎች

4.5.1. በማዕከሏ ያለው የስፖርት ሜዳዎች፣የህጻናት መጫዎቻዎችና ክፍት ቦታዎች የሚሸፍኑት ቦታ ምን ያህል ነው?

……………………………………………………………………………

4.5.2. በማዕከሏ ያሉ የስፖርት ሜዳዎች እና የህፃናት መጫወቻ ክፍት ቦታዎች በቂ ናቸው ?

…………………………………………………………………………………

4.5.3. ተጨማሪ የስፖርት ሜዳዎች እና የህፃናት መጫወቻ ክፍት ቦታዎች ያስፈልጋሉ?

…………………………………………………………………………………

# እዝል 2 - መረጃዎችን ለመተንተን የምንጠቀምባችው ፎርሙላዎች

1. የተለያዩ ሰብዓዊ እና ተፈጥሮአዊ በሆኑ ጉዳዮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለመተንተን የሚጠቅሙ ፎርሙላዎች

**ጥግግት**

- Crude population density = $\frac{\text{Total population}}{\text{Total area (km}^2\text{)}}$

- Agricultural density = $\frac{\text{Rural population}}{\text{Cultivated land (km}^2\text{)}}$

- Physiological density = $\frac{\text{Total population}}{\text{Cultivable land (km}^2\text{)}}$

**የአካባቢው የተዳፋትነት መጠን**

የአካባቢውን የተዳፋትነት መጠን ለማወቅ በቅድሚያ የሚከተሉትን መረጃዎች እና መሣሪያዎችን መያዝ ያስፈልጋል

1. ኮንቱር ማፕ
2. ማስመሪያ

እነዚህ መሠረታዊ ነገሮችን በመያዝ በሚከተሉት ቅደም ተከተል ደረጃዎች የተዳፋትነት መጠኑን ማስላት ይቻላል

i. Get base map with contour lines ,

ii. Classify & delineate contour lines with similar spacing,

iii. Measure horizontal distance (H.D) using scale(ruler),

iv. Identify vertical interval (V.I) , and employ the following formula:

$$\text{Slope} = \frac{\text{vertical interval}}{\text{Horizontal Distance}} \times 100$$

percentage and if x60 in terms of degree

**የተፈጥሮ አማካይ የሙቀት እና የዝናብ መጠን**

እነዚህን መረጃዎች በተመሳሰይ ከፍታ ላይ ከሚገኙ የአየር ፀባይ መመዝገቢያ ማዕከላት ማግኘቱ ጠቃሚ ነው

አስፈላጊ የአየር ፀባይ መረጃዎች

- የገጠር ማዕከሉ አማካይ የሙቀት መጠን
- የገጠር ማዕከሉ አማካይ የዝናብ በጠን
- የገጠር ማዕከሉ የአየር ፀባይ ዞን

## እዝል 3 ፦ ለተለያዩ የመሬት አጠቃቀም ድልድል የቦታ ምርጫ መስፈርት

**3.1. በመሬት አጠቃቀም ድልድል ውስጥ የመኖሪያ አካባቢዎን ለመወሰን የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ያስፈልጋል:** የመኖሪያ አካባቢዎች

- ጥቁር መረሬ አፈር በሚገኙባቸው አካባቢዎች ባይሆኑ ይመረጣል
- የመሬት እጥረት ካላጋጠመ በስተቀር የመኖሪያ ሰፈሮች በገጠር ማዕከሉ ክልል በሁሉም አካባቢ እንዲኖር ማድረግ::
- መጠነኛ ተዳፋትነት ባሉባቸው አካባቢዎች እንዲሆኑ ማድረግ፤ የተዳፋትነት መጠናቸው ከ1% - 15% ሊመረጥ የሚችል ቢሆንም ከ1% - 10% ቢሆን ግን በጣም ይመከራል
- የተፈጥሮ አደጋዎች ከሚፈጠሩባቸው አካባቢዎች በጣም የራቁ መሆን አለባቸው ለምሳሌ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የመሬት መንሸራተት፣ የተፈጥሮ በሽታዎች፣ ወረርሽኞች እና የመሳሰሉት::

**3.2. በመሬት አጠቃቀም ድልድል ውስጥ የንግድ አካባቢዎን ለመወሰን የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ያስፈልጋል:**

**የንግድ አካባቢዎች በሚከተሉት አካባቢዎች እንዲሆኑ ይመከራል**

- በገጠር ማዕከሏ ማዕከል እና በማዕከል አቅራቢያ
- በዋናዋና መንገዶች ዳርቻ,
- በዋናዋና መንገዶች መጋጠሚያ

**3.3. በመሬት አጠቃቀም ድልድል ውስጥ የአስተዳደር ተቋማት አካባቢዎች ምርጫ በሚከተሉት ነጥቦች ሊወሰን ይችላል**

- በሁሉም አቅጣጫ
- በመጋቢ መንገድ ዳርቻዎች
- ከንግድ ማዕከላት የራቁ መሆን አለባቸው

## 3.4. በመሬት አጠቃቀም ድልድል ውስጥ የአገልግሎት ተቋማት አካባቢዎች ምርጫ

### A. የትምህርት ተቋማት አካባቢዎች ምርጫ

- ለመኖሪያ ሰፈሮች የቀረቡ መሆን አለባቸው
- የተዳፋትነት መጠናቸው ዝቅተኛ ሆኖ ከ1-10% ቢሆን ይመከራል
- የተፈጥሮ አደጋዎች አና ወረርሽኞች ከሚከሰቱባቸው አካባቢዎ የራቁ መሆን አለባቸው
- ከድምፅ በካይ ተቋማት እና ከንግድ ማዕከላት የራቁ መሆን አለባቸው

### B. የማምለኪያ ሥፍራዎች

- ለዋና መንገዶች የቀረቡ መሆን አለባቸው
- በቦታ ላይ ሥርጭት ተመጣጣኝ መሆን አለበት
- ለትምህርት እና ጤና ተቋማት የቀረቡ መሆን የለባቸውም

### C. አገልግሎቶች

- የፖስታ እና የስልክ አገልግሎት መስጫ ተቋማት በገጠር ማዕከላት ማዕከል ሆኖ ለገበያ እና ለንግድ የቀረቡ መሆን አለባቸው
- በዋና መንገዶች ዳርቻዎች ላይ መሆን አለባቸው

## 3.5. የኢንዱስትሪ እና የመጋዘን ሥፍራዎች

- በካይ እንዱስትሪዎች ከንፋስ አቅጣጫ በተቃራኒ አካባቢዎች መልማት አለባቸው
- በካይ እንዱስትሪዎች ከመኖሪያ፣ ከትምህርት እና ከጤና ተቋማት የራቁ መሆን አለባቸው
- የገጠር ማዕከሏን ውበት ለመጠበቅ በሚያስችል ሁኔታ መልማት አለባቸው

**3.6. የመዝናኛ ሥፍራዎች**

➔ በቦታ ላይ ያለቸው ስርጭት እኩል ሆኖ ለመኖሪያ አካባቢዎች በተመጣጣኝ ርቀት ላይ መሆን አለባቸው

➔ የመዝናኛ ስፍራዎች የተዳፋትነት መጠናቸው ዝቅተኛ (1-10%) ሆነው ከረግረግማ ቦታዎች የፀዱ ቢሆኑ ይመረጣል

**3.7. የግብርና ሥፍራዎች**

➔ የእርሻ ሥፍራዎች ውሃማ አካባቢዎች እንዲሆኑ ይመከራል

➔ የእንስሳ እርባታ ቦታዎች በነፋስ አቅጣጫ ላይ መሆን የለባቸውም

➔ የግበርና ሥፍራዎች የተዳፋትነት መጠናቸው ከ1-10% በሆኑ አካባቢዎች ቢሆን ይመረጣል

**3.8. ጥብቅ የአረንጓዴ እና የውበት ሥፍራዎች**

➔ ጥብቅ የአረንጓዴ ቦታዎች በተራራማ እና በወንዞች ዳርቻዎች አካባቢ ቢሆን ይመረጣል ነገር ግን የውበት ሥፍራዎች እንደአስፈላጊነቱ በአመቺ ቦታ ማድረግ ይቻላል

**3.9. ለተለየ ዓላማ የሚውሉ ሥፍራዎች**

➔ የተፈጥሮ አደጋዎች የሚበዙባቸው አካባቢዎች ለምንም ዓላማ መዋል የለባቸውም

➔ ወታደራዊ እና አደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ተቋማት በከተማው ክልል ውስጥ እንዲሆኑ ማድረግ.

➔ የባህል እና ቅርሳቅርስ ቦታዎች በገጠር ማዕከሏ አስተዳደር ጥበቃ ውስጥ መቆየት አለባቸው

**3.10. የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ ተቋማትን እና የአውቶቢስ ማቆሚያ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማጤን ያስፈልጋል:-**

**የአውቶቢስ ማቆሚያ**

- የአውቶቢስ ማቆሚያ ስፍራዎች በዋናው መንገድ አካባቢ ቢሆን ይመረጣል
- ከላይብራሪ፣ ከትምህርት እና ጤና ተቋማት የራቁመሆን አለባቸው
- የተዳፋትነት መጠናቸው ከ1 እስከ 5% በሆኑ ሜዳማ አካባቢዎች ቢሆኑ ይመረጣል
- የስልክ፣ የመብራት፣ የባምቡዋ እና የመሳሰሉት መስመሮች በተዘረጋላቸው አካባቢዎች መሆን አለባቸው
- የአውቶቢስ ማቆሚያዎች በገጠር ማዕከሏ ማዕከል አካባቢ ቢሆን ይመረጣል
- የቦታ በጠኑ የሚወሰነው እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በሚያስተናግደው ተሽከርካሪ መጠን መሰረት ነው

**3.11. የገበያ ማዕከላት ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማየት ያስፈልጋል:-**

- የገበያ ማዕከላት በገጠር ማዕከሏ አማካይ ቦታ ላይ መሆን አለበት
- ከመኖሪያ እና ከተለያዩ ሰፈሮች የሚነሱ የተለያዩ መጋቢ መንገዶች ባለው አካባቢ መሆን አለበት

- ከላይብራሪ፣ ከትምህርት እና ከጤና ተቋማት የራቀ መሆን አለበት
- የተዳፋትነት መጠኑ ሜዳማ ሆኖ ከ 1 እስከ 5%በሆነ አካባቢ ቢሆን ይመረጣል
- የቦታው መጠን እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ከፍተኛው የህዝብ ቁጥር በሚሰበሰብበት ወቅት ሊያስተናግድ የሚችል መሆን አለበት

**3.12. የእርድ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መሥፈርቶች ማየት**

- የእርድ ሥፍራዎች በከተማው ዳርቻ አካባቢ መሆን አለበት
- ለሥራው በቂ ቦታ ያለው መሆን
- ከውሃ ተፋሰስ መስመሮች የራቀ መሆን አለበት
- በንፋስ አቅጣጫ መሆን የለበትም

**3.13. የደረቅ ቆሻሻ መጣያ ሥፍራዎችን ለመወሰነ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማየት**

- ለዋናው መንገድ ከሁለት ኪሎሜትር ባልበለጠ ርቀት ላይ መሆን አለበት
- በነፋስ አቅጣጫ በኩል መሆን የለበትም
- የከርሰ ምድር ውሃ በሚገኙባቸው አካባቢዎች መሆን የለበትም
- ከውሃ ተፋሰስ መስመሮች የራቀ መሆን አለበት

**3.14. የዘላቂ ማረፊያ ሥፍራዎችን ለመወሰን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማየት:-**

- ከጤና፣ ከትምህርት እና ከመዝናኛ ሥፍራዎች የራቀ ሆኖ በዘላቂ ማረፊያ እና በከተማው መካከል ውስጥ የዳርቻ ክልል መኖር አለበት
- ሥፍራው መንገድ ሊኖረው ይገባል;
- የተዳፋትነት መጠኑ ከ10% በታች ቢሆን ይመረጣል
- የቦታው ስፋት እንደአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በየዕምነት ተከታዩ ባለው የሞት መጠን ይወሰናል